ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች

እናሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያለው አስተዋፅኦ ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

እጅጋየሁ በቀለ

በአማርኛ ትምህርት ክፍል ኤምኤ የማስተር ድግሪ ለማግኝት

ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለሚሟላት

የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ነሀሴ ፣2011ዓ.ም

ጅማ፤ኢትዮጵያ

# በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ ያለው አስተዋፅኦ

# ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ


እጅጋየሁ በቀለ

አማካሪ

ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ


ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቀረበ ጥናት


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና  ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች  እና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል



ነሀሴ ፣ 2011 ዓ.ም

ጅማ ፣ ኢትዮጵያ

# በጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽያለው አስተዋጽኦ ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች)

**የጥናቱ አቅራቢ ስም እጅጋየሁ በቀለ ፊርማ........ ቀን .................**

**የአማካሪ ስም................... ፊርማ....................ቀን..............**

**...................... ....................**

**የፈታኝ ስም..................... ፊርማ.....................ቀን...............**

**........................... .................. ..............**

# ምስጋና

ይህን ጥናት የተሳካ እንዲሆን ድክመቴንና ክፍተቴን እየሞሉ እንድሰራ በማበረታታትና አባታዊ ባህሪ ተላብሰው እረቂቆቹን በማናበብ የማስተካከያ ሃሳቦችን በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡በተጨማሪ በጥናቱ ዙሪያ በሀሳብ በቴክኖሎጅ እውቀት ችሎታቸውን ላጋሩኝ እና እንድጽፍ ላደረጉኝ ለወንድሜ ሰለሞን በቀለ ፣ለእህቴ ሚሚ በቀለ እንዲሁም ለቀኑ ፍቅሬ፣ ብዙዬ አጎናፍርና ወልደሃና እጅግሰማሁ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በተጨማሪ ወደዚህ ትምህርት ገብቼ ለዚህ ጥናትና ድህረ ምረቃ እንድደርስ ትምህርቱን እንድማር ህጻናት ልጆቼን በመያዝ አይዞሽ አለሁልሽ በማለት ሞገስ ለሆነችኝ ለምወዳት እህቴ እናኑ በቀለ እና ለውድ ባለቤቷ ተስፋዬ አድማሱ እንዲሁም በጣም ለምወዳቸው ልጆቻቸው በጸሎት ተስፋዬና ኪሩቤል ተስፋዬ ለእናቴ ለወ/ሮአበበች መኮንን ለወንድሞቼ፣ ለእህቶቼና ለባለቤቴ ጌታችን መዳኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ምኞታችሁንና ሃሳባችሁን ይሙላላችሁ፡፡ ኪዳነ ምህረት ከክፉ ነገር ጥላ ከለላ ሆና ትጠብቃችሁ፡፡

በመጨረሻም ይህንን ጥናት ለማከናወን አስፈላጊውን ወጭ ላሟላልኝና የድህረ ምረቃ ትምህርቱን እንድከታተል ለፈቀደልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡እንድሁም ሁሉን ነገር አስጀምሮ ላስፈጸመ አምላክ ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን፡፡

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመፃፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡የአጠናን ዘዴውም መጠናዊ (Quanitative Method) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከፊል ሙከራዊ ነው፡፡ተጠኝዎቹ በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ ትምህርት ቤት በ 2011ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተልላይ ያሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ሙከራው የተካሄደው ደግሞ በተራ የእጣ ናሙና የተመረጡ ሁለት ክፍሎች እያንዳንዳቸው 41 ተማሪዎችን የያዙ አጠቃላይ 82 ተማሪዎች ናቸው፡፡ እንደኛው 9ኛA የሙከራ ቡድን ሌላው 9ኛB የጥብቅ ቡድን ተብለው ተመድበዋል፡፡ ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበባቸው የተማሪዎች የድርሰት መፃፍ ፈተና፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ የተማሪዎች የድርሰት መፃፍ ፈተና ቅድመ ድርሰት መፃፍ ፈተና እና ድህረ ድርሰት መፃፍ ፈተና በመምህራን ታርመው በፅሁፋ ዙሪያ በሚነሱ የተለያዩ ሀሣቦች አንፃር ተተንትነዋል፡፡ ቅድመ ድርሰት መጻፍ ፈተና በሙከራ ቡድንና በጥብቅ ቡድን የተገኘውም አመካይ ውጤት በቁጥርና በመቶኛ እንዲሁም በመደበኛ ልይይት በቲ-ቴስት ''Independent Sample t-test''ተሰልቶ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና ደግሞ በሙከራ ቡድን በመደበኛ ልይይት ''Repeated Measures Sampl t-test'' ተሰልቶ የተገኘው ውጤትም ልዩነት መኖሩ እናበመምህራን ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ምክንያት የመጻፍ ችሎታቸው መሻሻሉ ተረጋግጧል፡፡ ከምጋቤ ምላሽ በኋላ በድህረ ድርሰት ፈተና ጥብቅ ቡድኑ ልዩነት ባለመኖሩ መሻሻል አለመኖሩ ስሌቱ አመልክቷል፡፡ አጠቃላይ ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማዳበር በኩል ያለውን አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጉት አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት፣ በርካታ ምጋቤ ምላሽ በአንደ ጊዜ አለመስጠት በዋንኛነት እንደሚጠቀሱ ተረጋግጧል፡፡

ይዘት ገጽ


ምስጋና.................................................................................. ..I

የይዘት ማውጫ ..........................................................................II

የሰንጠረዥ ማውጫ ....................................................................III

የአባሪዎች ዝርዝር......................................................................IV

አጠቃሎ ...................................................................................... V

ምእራፍ አንድ፤መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ .............................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ......................................................2

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች..........................................................3

1.4 የጥናቱ አላማ .........................................................................3

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ...............................................................4

1.6 የጥናቱ ወሰን ...........................................................................4

ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ይዘቶች ቅኝት ...................................................6

2.1.1 ድርሰት የመጻፍ ምንነት.........................................................6

2.1.2 የጽህፈት አስፈላጊነት ...........................................................8

2.1.3 የምጋቤ ምላሽ ጽንሰ ሃሳብ.................................................. 10

2.1.4 ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት የሚጤኑ መሰረታዊ ነገሮች............. 11

2.1.4.1 የጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት አቅጣጫ ........................................ 11

2.1.5 የምጋቤ ምላሽ አይነቶች ........................................................................ 12

2.1.5.1 ገምጋሚ ምጋቤ ምላሽ ........................................................................ 12

2.1.5.2 ትእዛዛዊ ምጋቤ ምላሽ ........................................................................ 13

2.1.5.3 አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ ........................................................................ 13

2.1.5.4 አስተካካይ ምጋቤ ምላሽ ........................................................................ 13

2.1.6 የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች ........................................................ 14

2.1.6.1 ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት ................................... 14

2.1.6.2 የታዩ ስህተቶችን በሙሉ ማረም ........................................................ 15

2.1.6.3 ከስህተቶች የተወሰኑትን መርጦ ማረም ............................................. 16

2.1.7 የምጋቤ ምላሽ ባህርያት ........................................................................ 17

2.1.7.1 አዎንታዊ ........................................................................................ 18

2.1.7.2 አሉታዊ ........................................................................................ 19

2.1.8 የውጤታማ ምጋቤ ምላሽ ባህርያት ......................................................... 20

2.2 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ........................................................................ 21

ምእራፍ ሶስት የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

የጥናቱ ዘዴ

3.1 የናሙና አመራረጥ ........................................................................ 24

3.1.1 የጥናቱ አካባይ ........................................................................ 24

3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ........................................................................24

3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ......................................................................25

3.1.4 የተጠኝ የተማሪዎእ ናሙና አመራረጥ...............................................................25

3.1.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ…………………………………………………….------------
25

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ...................................................................................26

3.2.1 የድርሰት መጻፍ ፈተና...................................................................................27

3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ .........................................................................................29

3.2.3 ቃለ መጠይቅ.................................................................................................30

3.3 የመረጃ አተናተን ...........................................................................................31

ምእራፍ አራት የጥናቱ ውጤየት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና.....................................................................................32

4.1.1 የድርሰት መጻፍ ፈተና ትንተና .......................................................................32

4.1.2 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና...............................................................51

4.1.3 የቃለ መጠይቅ ትንተና .................................................................................55

4.2 የጥናቱ ውጠየት ማብራሪያ...............................................................................60

ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና ስተያየት

5.1 ማጠቃለያ ......................................................................................................63

5.2 አስተያየት......................................................................................................66

ዋቢ ጽሁፎች ......................................................................................................67

አባሪዎች.............................................................................................................72

## የሰንጠረዥ ርእስ

የሠንጠረዥ ቁጥር ገጽ

1. በይዘት ላይ ተመስርተው የተሰጡ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላ......35

2. በአደረጃጀት ላይ ተመስርተው የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ

ሲሰላ .......................................................................................................38

3. ቃላትን በተመለከተ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላ... .....................41

4. በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተመስርተው የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላ.

..........................................................................................................................44

5. በቅርጽ ችግሮች ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላለ ....................46

6. አጠቃላይ የሙከራ ቡድንና የጥብቅ ቡድን አማካይ ውጤት...................... ....................48

7. የቅድመ ድርሰት ፈተና የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በ"Independent

sample t-test for Control and Experimental group".......................................49

8. የድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በ"Independent

Sample T-test for Control and Experimental group"..................................49

9.በጥብቅ ቡድንና በሙከራ ቡድን መካከል ያለ የድርሰት መጻፍ ፈተና ውጤት

ልዩነት በ"Repeated Measures Sample T-test"..................................50

11.የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና በመቶኛ ሲሰላ.............................51

12. የመምህራን አጠቃላይ መረጃ...............................................................56

## የአባሪዎች ዝርዝር

አባሪ -ሀ- ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ..................................................73

አባሪ -ለ- ለተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ............................................................75

አባሪ -ሐ- ለመምህራን የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ..............................................78

አባሪ -መ- በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ የወገሬ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘር ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ........................................97

አባሪ ረ በመምህራን ታርሞ የተሞላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት አያያዝ የሚያሳይ ናሙና ..........................................................................................................................100

አባሪ ሰ በመምህራን ታርሞ የተሞላ የጥብቅ ቡድን ተማሪዎች ውጤት አያያዝ የሚያሳይ ናሙና ..........................................................................................................................101

አባሪ -ሸ በመምህራን ታርሞ የተሞላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች

የድርሰት ፈተና ውጤት ..........................................................................102

አባሪ -ሸ- በመምህራን ታርሞ የተሞላ የጥብቅ ቡድን ተማሪዎች የድርሰ

ፈተና ውጤት ..........................................................................................104

አባሪ -ቀ- በመምህራን ታርመው የተመለሱ የድርሰት ጽሁፍ ፈተና ናሙና..................108

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የጽሕፈት ክሂል በተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ጥረት ናበኪሂ ልመገልገልን እንዲሁም የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቢ ምላሽን በመማሪያ ክፍልና ከክፍል ውጭ ልምምድ ማድረግን ይጠይቃል።ጽሁፍ አእምሮንና አካልን ማቀናጀት የሚፈልግና ከማሰብ ጋር የተያያዘ ተግባር ሲሆን በአንድ ጊዜም በርካታ ባህሪያቱን /ለምሳሌ፣ ይዘቱን፣ ቅርጹን፣ አላማውን፣ ተደራሲውን ወዘተ ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ በጸሀፊውና በአንባቢው መካከልም በሌሎቹ ተግባቦታዊ ክሂሎች እንደሚታየው አይነት ፈጣን ምላሽ አይገኝም ፡፡ጸሀፊው በድጋፍ ሰጭ ተግባቦታዊ ዘዴዎች ማለትም በአካል እንቅስቃሴ በፊት ገጽታ ፣በድምጽ ከፍታና ዝቅታ የማይጠቀም በመሆኑ ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና ስነ አእምሮአዊ ችግሮች የሚከሰቱበት ነው።(Byren 1991) እነዚህ ባህሪያት ደግሞ ክሂሉን በመማር ማስተማር ሂደት ዉጤታማነት ላይ የየራሳቸዉን ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ መገመት ይቻላል፡፡ በጽሕፈት ክሂል የመገልገል ችሎታ እንዲዳብር ለትምህርቱ ትኩረት መስጠት በቂ ዝግጅትና ልምምድ ማድረግ እንደሚገባ (Norrish1990:63) ይገልጻሉ::

መምህራን የጽህፈት ክሂልን በማስተማር ወቅት ጽህፈት መማርን ማመቻቸትና መከታተል የተማሪዎችን የጽሁፍ ተግባቦታዊ ክህሎት ማዳበር፣ የተማሪዎችን ጽሁፍ ማንበብና መገምገም በአጻጻፍ ሂደት ተማሪዎች በማሰላሰል በማቀድ፣ በማርቀቅና በመከለስ እንዲያልፉ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸዉ (Hedge1991) እና (Leki 1996) ያስገነዝባሉ፡፡ Richards (1990) በበኩላቸዉ መምህራን ተማሪዎች ትክክለኛ ጽሁፍ እንዲጻፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የተዋጣለት የመጻፍ ብልሀት ለመከተል እንዲችሉ ነገሮችን ማደራጀት እና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸዉ ይላሉ፡፡ ተማሪዎችን በክሂሉ በቂ እዉቀት አግኝተዉ ጽህፈትን (ድርሰትን) በቅርጹና በይዘቱ የተሟላ ሊያደርግ የሚችለዉን የአጻጻፍ ብልሀት አዉቀዉ መጻፍ እንዲችሉ መምህራን የተለያዩ የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን ቢጠቀሙ ያቀዱት ዉጤት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

Celce Murica (1991) እንደገለጹት ለጽህፈትትምህርትውጤታማነት ተጠቃሽ መንስኤዎች

የቋንቋመምህሩመርህትምህርቱንተግባራዊማድረግለክፍለጊዜውየሚሆኑትምህርቶችንማዘጋጀ ትተማሪዎች እንዲጽፉ የሚያደርጋቸውን ሁኔታ ማመቻቸትና ለሚጽፉት ጽሁፎች ተገቢ የሆኑ መጋቤ ምላሾችን መስጠት የሚሉትን ነጥቦች አስፈላጊነታቸውን አምኖ ከተገበራቸው የቋንቋ ተማሪ ራሱን ሊያሻሽልና የኪሂሉ ባለቤት ሊሆንያስችለዋል፡፡በተለይምምጋቤ ምላሽ የውጤታማ አደረጃጀት ግብአት ነው፡፡

የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መዳበር በስርአተ ትምህርት ወይም በመምህራን መልካም ፈቃድና ፍላጎት ብቻ የሚሰምር ነገር አይደለም የተማሪዎች ፍላጎትና በድርሰቱ መጠመድ ለውጤታማ ፅሁፋቸው በጣም ጠቃሚ ቁልፎች ናቸው (Walvoord፡ 1986)፡፡ ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት አውድ ቢፈጠርም አስፈላጊ የሆኑ ተስማሚ የትምህርት ሁኔታዎች ቢሟሉም ተማሪዎች እኩል የሆነ የድርሰትችሎታ ተፈጥሮአዊ መሰረት ያለውና በውጫዊ ሁኔታዎች መሟላት ብቻ የሚበለጽግ አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጅ ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ዝግጅት፤ የልምምድ መጠን ፤የጽህፈት ኪሂል ማዳበሪያ መልመጃዎች አዘገጃጀት ሁሄታ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አይነት የምዘናና ግምገማ ስልቶች በተማሪዎች የድርሰት ችሎታ መዳበር ላይ ሰፊ ሚና አላቸው፡፡

እንደ ምሁሩ አገላለጽ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ተማሪዎች ጽሁፍ እንዲጽፉ በማበረታታትና ለሚጽፉት ጽሁፍ ምጋቢ ምላሽ መስጠት ስህተታቸውን ለማየት ይረዳቸዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝዋ ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳት ኣበይ ጉዳይ በመንዝ ላሎምድር ወረዳ በወገሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለረጅም አመት በምታስተምርበት ጊዜ ያጋጠሟትን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ነው።ይኸውም ተማሪዎች ሃሳባቸውን አውጥተው በጽሁፍ የማሰቀመጥ ችሎታችው ኣናሳ መሆኑናተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት መምህራን የሚጠቀሙት ምጋቤ ምላሽ ስህተታቸውን አውቀው ለመለየትና ለማስተካከል የማያስችላቸው መሆኑናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡-

1.ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የድርሰት መጻፍ ችሎታ ያሻሽላልን?

2.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰቶች ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽትኩረት ምን ላይ ነው?

3. መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰቶች ላይ የሚሰጧቸውንፅሁፋዊ ምጋቤምላሾች አዎንታዊገጽታዎች አሏቸው?

4.የቋንቋመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ረገድ ምን ስልት ይጠቀማሉ?

5.ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ከተሰጣቸው ተማሪዎችና ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ካልተሰጣቸው ተማሪዎች መካከል ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ልዩነት አለ?

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጧቸው ጽሁፋዊምጋቢ ምላሾች የመጻፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውንአስተዋጽኦ መተንተን ነው፡፡በዚህመሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች ይዟል፡፡

1. በፅሑፋዊ ምጋቤ ምላሽየተማሪዎችን የድርሰት መጻፍ ችሎታ መሻሻል አለመሻሻሉን መፈተሽ
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰቶች ላይ ከሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ውስጥ የተማሪውን የድርሰት መጻፍ ችሎታ ለማዳበር ይበልጥ የሚረዳውን ምጋቤ ምላሽ መለየት፡፡
3. መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰቶች ላይ የሚሰጧቸው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ መለየት፡፡
4. የቋንቋ መምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ረገድ የሚጠቀሙትን ስልት መለየት፡

5. ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እና ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ባለመስጠት መካከል ያለውን የድርሰት ጽሁፍ ልዩነት መፈተሽ፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

1. ተለምዷዊውየድርሰት አስተራረም ዘዴ ማለትም ገምጋሚ ምጋቤ ምላሽ የነበረውን በመለወጥ አስተካካይና አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽን መምህራን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡
2. ከፅሑፋዊ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አይነቶች እና ስርአቶች ጋር መምህራን በማስተዋወቅ አማርኛ ድርሰትበማስተማርረገድወቅታዊየምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎችን ለመምረጥና ለመተግበር ያግዛል፡፡
3. የቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የድርሰት አጻጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ከመደበኛ ተግባራቸው በተጨማሪ የተለያዩ ስልቶችን በመቀየስ የድርሰትመጻፍና ማስተማር ስራበሙያዊ ስሜትና ሀላፊነት እንዲያከናውኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
4. በመርሀ ትምህርት፡በማስተማሪያ መፅሃፍትና ማቴሪያሎች ዝግጅት በቋንቋ መምህራን ስልጠና ረገድ የድርሰት ትምህርት አሰጣጥና ፅሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ በሚገኝ የወገሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ በሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለሚጽፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ለመጻፍ ችሎታቸው መሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ መተንተን ላይ የሚያተኩር ነው፡፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አራቱንም ኪሂሎች ማለትም ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍን ያቀፈቢሆንም የዚህ ጥናት ልዩ ትኩረት የተሰጠው መጻፍ ላይ ሆኖ በገላጭ ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለው አስተዋጽኦ ላይ ያተኮረ ነው

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ-ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 ድርሰት የመጻፍ ምንነት

የተማሪዎች ድርሰት መጻፍ ችሎታ ማዳበር በስርአተ ትምህርት ወይምመምህራንበክፍለ ጊዜ ብቻ በሚያስተምሩት የሚሰምር ነገር አይደለም፡፡ የተማሪዎች ፍላጎትና የድርሰት መጻፍ ተነሳሽነት ለውጤታማ ጽሁፋቸውበጣምጠቃሚ ናቸው (Walvoort 1986)፡፡በአንድ የትምህርት ተቋም አስፈላጊ ና ተስማሚ የሆኑ ትምህርት ቢሚሉም፤ተማሪዎች እኩል የሆነ የትምህርት ችሎታ በውጫዊ ሁኔታዎች መሟላት ብቻ የሚበለጽግ አለመሆኑን ያስገነዝባል ፡፡ይሁን እንጅ ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ዝግጅት የልምምድ መጠን የጽህፈት ኪሂል ማዳበሪያ መልመጃዎች አዘገጃጀት ሁኔታ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ አይነት የምዘናና ግምገማ ስልቶች በተማሪዎች የድርሰት ችሎታ መዳበር ላይ ሰፊ ሚና አላቸው፡፡

Raimes (1983) እና Kroll (1990) እንደሚያስረዱት ከ1970 በፊት መጻፍ በውጤት ላይ የተመሰረተ ሲሆን መምህራን ለተማሪዎቻቸው የአጻጻፍ መመሪያን ይሰጣሉ እንጅ ተማሪዎች ደረጃ በደረጃ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ርእስ ለመምረጥና ሀሳብ አፍልቆ ለመጻፍ ይቸገራሉ፡፡መምህራን ተማሪዎች ለጻፉት ጽሁፍ ውጤት ሰጥተው ማለፍ እንጅ በተማሪዎች የመጻፍ ኪሂል ላይ ለውጥ ሳያመጡ ቆይተዋል ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ይህ አይነቱ የጽህፈትትምህርት አቀራረብ እንዲቀየር ባደረጉት ጥረት ከ1971 ጀምሮ በተነሳው አብዮት የትምህርት አቀራረብ ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር እንዲቀየር ተደርጓል ፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ይህ አመለካከት ዳብሮ በተማሪዎች የጽሁፍ ስራ ውስጥ መምህራን ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ (Hyland 2003) እንደገለጹትም ጽህፈትን በሂደታዊ አቀራረብ በማስተማር ወቅት ተማሪው በመምህሩ ላይ ያለው ጥገኝነት ጎልቶ እንደሚታይ የሚያግዝ ነው፡፡

ፅሀፊትን ከሌሎች ኪሂሎች ይልቅ አስቸጋሪ የሚያደርጉት ባህርያቱ ፡-ስነ-ልቦናዊነቱ ፤ስነ-ልሳናዊነቱናአእምሮታዊነቱ ናቸው፡፡ በጽህፈት ክንውን ወቅት አንባቢን ማሰብ የማይቀር ተግባር ነው፡፡መልእክቱ ለአንባቢ እንዲደርሰው ፀሀፊው ይጨነቃል፡፡(Hedege 1988)::

ጽሕፈት በእይታዊ (Visual) ትምህርቶች (Symbols) ውክልና በመገልገል ሰዎች ሀሳብ የሚለዋወጡበት ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው፡፡ በመተላለፊያ ስልቱ ዕይታዊ ፤በአካላዊ ትግበራው አፍላቂ፤በተግባቦታዊ ባህሪውም ርቱዕ ኪሂል ነው (Widdowson፥1978፥ Harmer፥1991)::ፅህፈት በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተደረሰበትን ወይም የተጨበጠን ዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን አዲስ ሀሳብ ማፍለቂያ መንገድና ብልሀት ነው (Condon and Butler:1997)::

Pincas (1982) ፅህፈትን ሲገልፁ በትምህርት አማካኝነት የሚቀሰምና ደረጃውን ጠብቆ ከሚደረግ ተከታታይ ልምምድ የሚገኝ ችሎታ ነው፡፡ከዚህ ችሎታ ጋርም ፅህፈት አእምሮንና እጅን በማስተባበር ሀሳብን በተገቢ ምልክቶችና ቃላት በመወከል ለአንባቢ የግልንም ሆነ የጋራ ገጠመኝን የማካፈል ችሎታ ነው ብለዋል፡፡እንዲሁም (Jordan1991) ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ፅህፈት የሰው እውቀቱን ምኞቱን ሀሳቡን ወዘተ…ለመሰሎቹ ለመግለጽ የሚጠቀምበት የሚታይና ተቀባይነት ያለው ምልክት ነውይላሉ፡፡

ፅሕፈት ሀሳብን በትምህርት ወይም በቋንቋ የመወከል ሂደት ነው፡፡ሂደቱም አካልንና አእምሮን በማቀነቀጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህሪያቱን (ለምሳሌ ይዘትን የአጻጻፍ ስልትን የጽሁፍ መዋቅርን የቃላት ምርጫን የሀሳብ አንድነትን ግጥምጥምነትንና ተከታታይነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወንና ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው(Nunan;1989)::

ከምሁራን ሀሳብ የምንረዳው የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ናየሚያስበውን ነገርእንዲሁም እውቀትና ገጠመኙን በአጠቃለይ በጽህፈት አማካኝነት በሚገልጽበት ጊዜ መልእክቱ ለአንባቢው በተገቢው መንገድ ለማስጨበጥ የመጻፍ ችሎታን በማሻሻል የሚከናወን ሂደታዊ ተግባር መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.2 የፅህፈት አስፈላጊነት

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በጽሁፍ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በርካታ ናቸው፡፡ስለሆነም የሚሰጧቸውን ጽሕፈት ነክ ስራዎች በጽሁፍ አቀነባብረውና አደራጅተው መስራት እንዲችሉ ጽህፈትን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡ከዚህ አንጻር የጽህፈትወይም የድርሰት ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን ሀሳቦች ሰንዝረዋል፡፡እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

Wigand(1986) "ተማሪው መጻፍ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ በሚጽፍበት ጊዜ የጽህፈት ተግባቦትን አላማ ለይቶ በማወቅ ክሂሉን በአግባቡ መጠቀም እንዲችል በቂ የጽህፈት ትምህርትያስፈልገዋል፡፡በትምህርት ወቅት ለምን እንደሚጽፍለማን እንደሚጽፍ እንዴት እንደሚጽፍ በመጠየቅ እንደሚጻፍበት አላማ የመጻፍ ክሂሉን የሚያዳብረው ጽህፈትን ሲማር ነው" በማለት ጽህፈትን የማስተማር አስፈላጊነት ይገልጻሉ፡፡

Raimes(1983) በበኩላቸው ጽህፈትን መማር ተማሪዎች ሌሎች የትምህርት አይነቶችን እንዲማሩ ከማገዙም በላይ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ አገባቦችንና አገላለጾችን ፈሊጣዊ አባባሎችንና ቃላትን እንዲያውቁ ከመርዳቱም በላይ በተማሪዎች ዘንድ የመማር ተነሳሽነትን ይፈጥራል፡፡ከዚህ በተጨማሪ Venkateswaran (1995) "የጽህፈት ክሂል ትምህርት ተማሪዎች በቃል የሚሰጣቸውን ትምህርትአዳምጠውና የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ማስተዋሻእንዲይዙና በቤት ስራና በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ጽሁፍ ነክ መልመጃዎች በጽሁፍ አቀነባብረው መግለጽያስችላቸዋል"እንደ Celce Murcia (1991) አገላለጽም ተማሪዎች የፊደል ቅርጽ በመለየት ቃላትን መስርተው የቃላት ምርጫናአጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ማስተላለፍ የሚችሉበትን የተግባቦትን ስርአት እንዲያውቁ ጽህፈትን ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

ከላይከቀረበው የምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በትምህርት ቤት ውስጥምሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ድርሰት እንዲጽፉ ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ የታላሚውን ቋንቋ ፊደል ከመለየት ጀምረው ሀሳባቸውን በብቃት መግለጽ እስከሚያስችላቸው ሰፊ የጽህፈት መዋቅር ድረስ መማር እንደሚያስፈልጋቸው ነው፡፡

የጽህፈት አስፈላጊነት ሰዎችን ከማግባባቱ ወይም ከቦታና ከጊዜ ውስንንት አልፎ አገልግሎት መስጠት ከመቻሉ አኳያ ብቻ የሚታይ አይደለም {Raimes:1983; White

and Arndt:1991)ጽህፈት ከተግባቦት መሳሪያነቱም ባሻገር የተለያዩ እውቀቶችን መቅሰሚያ ፤የሀሳብ ማሰባሰቢያና ማሳያ ሆኖ ያገለግላል፡፤ስለዚህም ጽህፈትን መማር ተማሪዎች የፈርጀ ብዙ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡Byren (1991) የጽህፈትን ትምህርት አስፈላጊነት ከሰነ-ትምህርታዊ (pedagogical) ከጠቀሜታው አኳያ የገለጹት የጽሁፍ ፈተናን ለመስራት ሌሎች ክሂሎችን ለመማርና በንባብ የሚከናወኑ የመማሪያ አውዶችን ለመፍጠር ያስችላል በማለት ነው፡፡

የጽህፈት ትምህርት አስፈላጊነት ከግለሰባዊናከማህበረሰባዊ ጠቀሜታዎች አኳያ ይታያል፡፡በዚህም መሰረት ጽህፈትን መማር ለግለሰቡም አመለካከቱን ለመግለጽና ለማሳወቅ እፅምሮአዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉሰነዶችን ለመመረመር ለማህበረሰቡም የጽሁፍ ቋንቋን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ የስነ-ጾሁፍ ስራዎችንና ልዩልዩ መረጃዎችን ለማጠራቀም የሚያገለግል መሆኑን(Bradley1994) ይገልጻሉ፡፡

Heaton(1991) በበኩላቸው ጽህፈትን ማስተማር በመደበኛ ትምህርት የሚዳብሩትን የጽሁፍ ተግባቦትን ለማካሄድ ሀሳብና ስሜትን ለመግለጽ የሚያስችሉትን የጽህፈት ክሂሎችን ማዳበር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡አክለውም ጽህፈትን ማስተማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ለማዳበር እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

አንደኛ ማስተላለፍ ለሚፈለገው ሀሳብ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ ፤የአረፍተ ነገር አመሰራረትና የአንቀጽን አወቃቀር ስርአት ጠብቆ የመጻፍ፤የተለመደና መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ብቃትን ያዳብራል፡፡

ሁለተኛ ሰዋሰዋዊ ክሂሎችን (Grammatical Skills) በመማር ተገቢየሆኑ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቶ የመጻፍ ብቃትን ያጎለብታል፡፡

ሶስተኛ ግላዊ ስሜትን ለመግለጽ የሚያስችሉ ቃላትንና ዐረፍተ ነገሮችን የማፍለቅ ችሎታን ያዳብራል፡፡

አራተኛ ተገቢ የሆኑ ቃላትን በመምረጥ አላማን ወስኖ ለአንባቢ የማቅረብ ብቃትንናየሀሳብ አደረጃጀትን ትክክለኛነትን ጠብቆ መረጃዎችንበቅደም ተከተል አቀናብሮ የመግለጽችሎታዎችን ያዳብራል፡፡

አምስተኛየጽሁፍ ቋንቋ መግለጫ የሆኑትን የስርአተ አጻጻፍ ደንቦችን ተገንዝቦ በተገቢውመንገድበአገልግሎትለይየማዋልብቃትን ያስገኛል፡፡

በመጨረሻም ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ተገቢና ተስማሚ የሆኑ ቃላትን መርጦ ማስተላለፍ የሀሳብ አቀራረብን ሚዛናዊነት ጠብቆ ክስተቶችን ወይምድርጊቶችን በቅደም ተከተል አቀነባብሮ የመግለጽ ችሎታ የማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡

Byme(1991)የጽህፈት ኪሂል ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ በጽሁፍ የተደገፈ ትምህርት በተማሪዎች ዘንድ የተነሳሽነትና በራስ የመተማመን ስሜትን ያጎለብታል፡፡ ተማሪዎችም በየትምህርት አይነቱም መሻሻል ማሳየታቸውን ያረጋግጣል በማለት ገልጸውታል፡፡በአጠቃላይ ከላይ ከተነሱት ሀሳቦች የጽህፈት ኪሂልን ማስተማር ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በአግባቡ ተጠቅመው ሀሳባቸውን በጽሁፍ አማካይነት እንዲገልጹ ለማስቻል በቋንቋው በሳል የአጠቃቀም ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተገቢ የሆኑ የቃላት አወቃቀሮችንና የቋንቋ አጠቃቀሞችን በጥቅም ላይ ለማዋል በእነሱና በአንባቢያቸው መካከል ጤናማ የሆነ መግባባት ለመፍጠርና በጽህፈት ክሂል ትምህርት ልምምድ ወቅት ሌሎች ኪሂሎችንም ጭምር እንዲያዳብሩምለማድረግ እንደሚረዳ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.1.3 የምጋቤ ምላሽ ጽንሰ ሀሳብ

እንደ ዋልተር ላምበርግ አገላለጽ ምጋቤ ምላሽ ተከታታይ የሆነ ክንውንን የሚነካ የተማሪዎችን ስሜት ወደ ተወሰኑ ጉዳዮች በመማረክ እነዚህኑ ጉዳዮች በተከታታይ ክንውን ውስጥ ለውጥ እንዲያካሂዱ የሚያደርግ የክንውን መረጃ (ዜና) ነው (Timbur, John 1985) ፡፡

Crystal,David (1994) አስተሳሰብ ምጋቤ ምላሽ ለኦርጅናሉ ውጤት አመንጭ መረጃ (ዜና) መልእክት የሚተላለፍበት ሂደት ነው፡፡መረጃው ወይም ዜናው ራሱ ምጋቤ ምላሽ ነው፡፡ቃሉከሳይበርኔትክስ የመጣ ሲሆን ለማሽኖች፡ለእንስሳትና ለሰው መገናኛ ውሏል፡፡መልእክት ላኪው መልእክት ተቀባዩ የተላለፈለትን መልእክት ስለመቀበሉ የሚቆጣጠርበትና አስፈላጊ ለውጦችን የሚያደርግበት ስርአት ነው፡፡

Keh,C,L(1990)እንደሚገልጸው ምጋቤ ምላሽ ለጽህፈት ሂደታዊ አቀራረብ መሰረታዊ አላባ ነው፡፡ተማሪው (ጸሀፊው) ጽሁፉን እንዲከልስ መምህሩ የሚሰጠው የመረጃ ግብአት

ነው፡፡በሌላ አነጋገር ጸሀፊው አንባቢን የሚስብ ጽሁፍ እንዲያቀርብ የሚያገኘው አስተያየት ጥያቄዎችና ሀሳቦችን ይመለከታል፡፡

## 2.1.4 ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት የሚጤኑ መሰረታዊ ነገሮች

### 2.1.4.1 የፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት አቅጣጫ

እንደ Fathman and Whalley (1990) ገለፃ አንድ አንድ መምህራን ለስርዓት ነጥብ፣ ለፊደል አጣጣል፣ ለሰዋሰው አገላለፅና ለመሳሰሉት ትኩረት ሲሰጡ አንድ አንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ለይዘት አደረጃጀት ቅድሚያ ይሰጣሉ ፡፡ ስለዚህ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ትኩረት የተለያየ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ፅሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ቅርጽንይዘትን ወይም ቅርጽንና ይዘትን በጥምረት መሆን አለበት የሚለው ቁርጥ ያለ መደምደሚያ ያልተሰጠው ነው፡፡ በቅርጽ ዙሪያ የሚያነጣጥር ምጋቤ ምላሽ፣ በሆሄያት ግድፈት በስርዓት ነጥብና በቃላት ተገቢነት በዓረፍተ ነገር አመሰራረት በአንቀፆች ስረትና  በሰዋሰው ህግጋት ትክክለኛ መሆን ላይ ትኩረት ያደረጋል ( Keh 1990 Zedge 1988) ፡፡  በተጨማሪም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባር ለማለፍ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን በትክክል ማዋቀርና ማፍለቅ በመቻልና ባለመቻላቸው ላይ አጽንኦት በመስጠት እርማት የሚደረግበት ስልት ቅርፅን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መምህራን ምጋቤ ምላሻቸው ከይዘት ይልቅ በቅርጽ  ላይ ትኩረት ማድረጉ ለመፃፍ ኪሂል መሻሻል የተሻለና ትክክለኛ አካሄድ እነደሆነም (Lek 1990 Cohen and Cavalcant 1990 Zamel 1985) ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል Shih (1986) እንደሚያስረዱት ለይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለተማሪዎች የፅሁፍ ልምምድ በመምህራን የሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ የተዋጣለት የሚሆነው የፅሁፉን ይዘት መሰረት ካደረገ ነው፡፡ይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ ማለት ደግሞ የተማሪዎችን የጽሁፍ መልመጃ ከሀሣብ አንድነት አደረጃጀትና ጥልቅት ከመሳሰሉት አንፃር ታይቶ አስተያየት የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡

በተጨማሪ በይዘት ላይ ትኩረት ተደርጐ የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ በአብዛኛው በትርጉም ወይም በፍቺዙሪያ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም መልዕክቱ የቀረበበት ቋንቋ ወይም ሰዋሰው ቅንብሩ ጥሩ ነው ባይሰኝም ይዘቱ በተገቢ ሁኔታ ከተደራጀ ከሌላ ሰው ጋር

መግባባት እንደሚያስችል ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ይዘትን ትኩረት የሚያደርግ ምጋቤ ምላሽ አስፈላጊና ላቅ ያለ ቦታ እንደሚሰጠው ያሳያል (Shih 1986)

Fathman and Whalley (1990) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ደግሞ መምህራን ለይዘት በተናጥል ምጋቤ ምላሽ ከሰጡባቸው ጽሑፎች የበለጠ ይዘትንና ቅርፅን አስመልክተው ጥምር ምላሽ የሰጡባቸው ፅሁፎች በይዘታቸው ላይ የተሻለ መሻሻል፤ አሳይተዋል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ፅሑፎቻቸውን የበለጠ የሚያሻሽሉት ቅርፅንና ይዘትን በማጣመር ምጋቤ ምላሽ ከተሰጠ መሆኑን መምህራንሊረዱት ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይዘትንና ቅርፅን ያጣመረ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ(Grami 2005) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ምጋቤ ምላሽ በቅርፅ፣በይዘት እንዲሁም ሁለቱን በጥምረት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በብዙ ምሁራን ዘንድ መስማማትን ያገኘው ቅርፅንና ይዘትን ያጣመረ ምጋቤ ምላሽ ተመራጭነት ይኖረዋል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ በቅርፅና በይዘት መካከል የተሳሰረ ዝምድና በማንኛውም ጥሩ ፅሁፍ ውስጥ የሚታይ ጉልህ ግንኙነት አንዳላቸው ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀም ተገቢ ነው (Taylor 1981)

## 2.1.5የምጋቤ ምላሽ አይነቶች

ምጋቤ ምላሽን በተለያየ መንገድ መስጠት ይቻላል፡፡ ዋናው ነጥብ መምህራን አንዱን አይነት ለብቻው ወይም አንዱን ከአንዱ ጋር በማደበላለቅ የሚጠቀሙ ሲሆን እያንዳንዱ የምጋቤ ምላሽ አይነት የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ስላለው መምህራኑ ይህን ተረድተው በአጠቃቀም ጊዜ አስፈላጊውን ትኩረትና ጥንቃቄ መስጠት ይገባቸዋል (Anker 2001}::ከብዙዎቹ መካከል በዋናነት የሚጠቀሱትን የምጋቤ ምላሽ አይነቶች የሚከተሉት እንደሆኑ (Angelo and Cross 1993:Dalker 1989:Moxley 1988} ይገልጻሉ፡፡

### 2.1.5.1ገምጋሚ ምጋቤ ምላሽ

ይህ የምጋቤ ምላሽ አይነት በውጤት የሚገለጽ ነው፡፡መምህራን ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሁፍ ተገቢ ይሆናል ያሉትን ውጤት የሚሰጡበት ሲሆን ተማሪዎቹም በመምህራቸው የተሰጣቸውን ውጤት በማየት የጽሁፋቸውን ደረጃ ጥሩ ወይም ዝቅተኛ መሆኑን

ይገነዘቡና በቀጣይ ስራቸው የጎደለውን ውጤታቸውን ለማስተካከል ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚያበረታታ ነው፡፡ (Daiker 1989)

### 2.1.5.2 ትእዛዛዊ ምጋቤ ምላሽ

ትእዛዛዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ልምምድ ስራ ላይ ያሉትን ወይም ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስህተቶችን እንዲያስተካክሏቸው በመምህራን ከሚሰጡት አስተያየቶች ይልቅ ተማሪዎች ራሳቸው ስህተታቸውን እንዲያርሙ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ዘዴው ተማሪዎች ምን አይነት ስህተት እንደፈጸሙና እንዴት መታረም እንዳለበት እንዲያውቁ የሚረዳቸው ቢሆንም ተማሪዎች ብዙ ድካም ስለማይፈልጉ ተቀባይነቱ አነስተኛ ነው ፡፡ (Daiker 1989)

### 2.1.5.3 አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ

Moxley(1989) አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ጽህፈት ላይ የሚሰጠው በጥያቄዎች መልክ ነው፡፡ጥያቄው ሲቀርብ ጠቅለል ብሎ ሲሆን የሚያተኩረው በተወሰነ ነገር ላይ ብቻ ነው፡፡አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ ሲቀርብ የጽሁፉ ዋና ሀሳብ የቱ ነው?ጽሁፉ በምን ላይ ያተኩራል? የተሰጠው ማጠቃለያ ተገቢ ነው? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል፡፡በተጨማሪም ይህ ዘዴ ከጽሁፍ ቅርጽ ይልቅ ለይዘት የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ነው፡፡

### 2.1.5.4 አስተካካይ ምጋቤ ምላሽ

አስተካካይ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው የሰዋሰው ስህተቶች መምህሩ በመጠቆም ተቀባይነት ያለውና ትክክለኛውን አስተካክሎ በመጻፍ የሚሰጥ እርማት ነው፡፡(Anglo and Cross 1993)::ይህ ዘዴ ሲተገበር ስህተት የሆነውን በማክበብ ወይም የተለየ ምልክት በማድረግ ሲሆን ስህተት የሆነው ቃል ሀረግን ዐረፍተ ነገርን በማጥፋት የቃላትና የሀረጋት አገባብ በማስተካከል የተዘበራረቀ የአረፍተ ነገሮችቅደም ተከተል አስተካክሎ በመጻፍና ያልተሟላ ቃል ወይም ሀረግ በጽሁፍ ውስጥ ከታየ አስፈላጊውን እየጨመሩ አስተካክሎ ምጋቤ ምላሽ መስጠትን ይጠይቃል (Daiker 1989)::አስተካካይና አጠናካሪ ምጋቤ ምላሾች ተቀናጅተው ቢሰጡ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ የተሻለ ለውጥ አለው፡፡በዚህ

ጥናትም ለማየት የተሞከረው አጠናካሪና አስተካካይ ምጋቤ ምላሽ አቀናጅቶ በመስጠት በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ ለውጥ ማሳየቱን ነው፡፡

## 2.1.6የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች

እንደ ምሁራኖች ገለፃ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነ ውጭ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲጽፉ ማድረግ እና ተገቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት የመፃፍ ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡ እነዚህ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች እንደሚከተለው ያሰፍሯቸዋል፡፡

### 2.1.6.1ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት

ይህ ዘዴ እንደ ተሻለአማራጭ የሚወሰድና የመምህሩን የስራ ጫናን ያቃልላል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን መምህራን ስህተቶችን በማመልከት የሚጠቀሙባቸው የምጋቤ ምላሽ ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት በሚለው የጽሁፍ ወይምየድረሰት ምጋቤ ምላሽ ዘዴመምህራን ሲጠቀሙ ተማሪዎቻቸው ለሁሉም ምልክቶች እንግዳ እንዳልሆኑና ሲያጋጥሟቸው አገልግሎት እንዳላቸው በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል (Hedge 1988፣Byme 1988 ፣ Raimes 1983) በተጨማሪ Byme(1988) ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት ምጋቤ ምላሽን ስንጠቀም ቀጠሎ ከተዘረዘሩት መምረጥና መገልገል እንደምንችል ያስረዳል፡፡ስህተት የሆነውን አሀድ በማስመር በጽሁፍ ጠርዝ ላይ ምልክቱን ማስቀመጥ

1.ስህተት የሆነውን አሀድ ለይቶ በማስቀመጥ ተጨማሪ ማብራሪያ አለመስጠት
2.በጽሁፍ ጫፍ ላይ የተመረጠውን ምልክት አስቀምጦ በስህተቱ ላይ ምንም አይነት ጥቆማ አለማድረግ፤
3.የተለየ ምልክት እያንዳንዱን ስህተት የሚጠቁም በጽሁፍ ጠረዝ ላይ ማስቀመጥ፤
4.ለሁሉም ስህተት ሊያገለግል የሚችል የተለየ ምልክት በጽሁፍ ጠርዝ ላይ ማስቀመጥና ስህተቶችን ግን አለመጠቆም የሚሉት ናቸው፡፡

ከላይ ካለው ሀሳብ የምንረዳው ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት የምጋቤ ምላሽ ዘዴ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ውስጥ ያለውን ስህተት አምነው በመቀበል በሚቀጥለው ጽሁፋቸው ችግራቸውን ቀርፈው እንዲጽፉ ከማድረጉም በተጨማሪ

የተማሪዎችን አእምሮ በማይነካ መልኩ ስህተቶችን መጠቆሙ በሚቀጥለው ጽሁፋቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

Byrne (1988) ገለጻ ደግሞተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ላይ ስለሰፈሩት የተለያዩ ምልክቶች የተማሪዎችን ጽሁፎች በማረም በኩል ችግሮችን ሙሉ በሙሉ በአንድ ጊዜ የሚቀርፍ ሳይሆን በተደጋጋሚ በመጻፍ ከስህተታቸው ለመውጣት ጥረት እንዲያደርጉ የሚረዳ እንደሆነ የሚያመላክት ምጋቤ ምላሽ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

## 2.1.6.2 የታዩ ስህተቶችን በሙሉ ማረም

Lalande (1982) ይህን የጽሁፍ የማረም ዘዴ አጠቃላይእርማትመሆኑንና ምላሹ ጥንታዊ የአስተራረም ዘዴ በመባልም እንደሚታወቅ ይገልጻሉ ፡፡ይህ የምጋቤ ምላሽ ዘዴ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ላይ የሚታዩትን ማንኛውንም ስህተቶች አንድ በአንድ እየነቀሰ በማሳየት ምጋቤ ምላሽ የሚሰነዘርበት ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Byrne (1988) በጽሁፍ ውስጥ ለሚታይ ለማንኛውም ስህተት ምጋቤ ምላሽ የሚሰጥ ከሆነ ተማሪዎች ብዙ ስህተቶችን በመስራታቸው እንዲያፍሩ ፤እንዲሸማቀቁና ከጓደኞቻቸው ያነሱ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ስለሚቆጥሩ በመምህሮቻቸው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል ፡፡ይህ ደግሞ የመጻፍ ተነሳሽነታቸውንና ዝንባሌያቸውን ስለሚያሳጣቸው ትምህርቱንም ሆነ መምህራንን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል ፡፡ስለሆነም በጽሁፍ ውስጥ ለሚታዩ ለማንኛውም ስህተት ምጋቤ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ከመጠን ያለፈ እርማት የሚደረግላቸው ከሆነ በርካታ ተማሪዎች ከመጻፍ ሊታቀቡ ይችላሉ ( Madson 1983)::

Gippsetal (2004) እና Edge (1988)እንደሚገልጹት ደግሞ ተማሪዎች በጽሁፋቸውለሚታዩ ስህተቶች ከሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ የበለጠ እንዲማሩ ስህተቶቻቸውን እንዲቀንሱ ና እንዲቀርፉ ከተፈለገ ምጋቤ ምላሹን ቀስ በቀስ መስጠት እንጂ በአንድ ጊዜ ለሚፈጽሙት ለእያንዳንዱ ስህተት የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ሆነ በመምህራን ላይ ጫናን የሚፈጥር ግራ መጋባትን የሚያስከትልና ተነሳሽነትን የሚቀንስ ነው፡፡ይህም

የምጋቤ ምላሹን ውጤታማነት ጥርጣሬ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡እንደ ምሁራኖቹ አገላለጽ ለተማሪዎቹ የሚሰጠው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ስህተት የሚያሳይ ስለሆነየመጻፍ ተነሳሽነትታቸውን ይቀንሳል ይህ እንዳይሆን ሙሉ በሙሉ ስህተታቸውን በግልጽ ሳናስቀምጥ በመጠኑ አቅጣጫን በመጠቆም ስህተት ማሳየት ካልተቻለ የመጻፍ ፍላጎታቸውን ማዳበር እንደማይቻል ገልጸዋል ፡፡

### 2.1.6.3 ከስህተቶች የተወሰኑትን መርጦ ማረም

ይህ ስህተት የማረም ዘዴ የሚከወነው የተወሰኑ ችግሮችን ብቻ መርጦ በማረም ሲሆን ጥቂት ስህተቶች የትኩረት አምድ ሆነው ይመረጣሉ ስህተቶቹ የሚታረሙት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈጽሟቸውና የቋንቋመማርን በሚያደናቅፉ አጠቃላይና ዋናዋና (Global errors) የጋራ ችግሮች ላይ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም መግባባትን ሊከለክሉ የሚችሉ ለሁሉም ወይም ለአብዛኛው ተማሪ የጋራ የሆኑ ዋና ዋና ስህተቶችን ማረም የጽሁፍ ስራን ውጤታማ ያደርገዋል ስህተቶችን መርጦ ማረም የሚከወነው ስህተቶችን ሁሉ የማረም ዘዴ በቋንቋመምህሩ ላይ የሚፈጥረውን ረጅም ጊዜ መሻማትና በቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚከሰተውን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመቅረፍ ታስቦ ነው(Byrne 1988: 124: Lalande 1982)::

እንደ Anker (2003) ገለጻ መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የሚታዩ ሁሉንም ስህተቶች የሚያስተካክሉበት ምክንያት ፡-

1.ተማሪዎች እንዲምታቱና ግራ እንዲጋቡ ስለሚያደርግ የሚፈጽሙትን ስህተት ለማሶገድ ተነሳሽነቱና ዝንባሌው ስለማይኖራቸው ፤

2.ምጋቤ ምላሹ ከመብዛቱ የተነሳ ተማሪዎች መምህራንንም ሆነትምህርቱን መጥላት እንዲጀምሩ ስለሚያደርጋቸው

3.ተማሪዎች ደካማእንዲሆኑና ለመጻፍ ብቁ እንዳልሆኑ አድርገውእንዲያስቡ ስለሚያደርግ

4.ለሁሉም ስህተቶች ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ብዙ ጊዜን ስለሚጠይቅ ፤

5.ተማሪዎች በጽሁፍቸው ለፈጸሙት ስህተት የተሰጠውን ምጋቤ ምላሽ ሊረሱት ስለሚችሉ የሚሉት ናቸው፡፡

ነገር ግን ስህተቶችን መርጦ ማረም ከስህተት የጸዳ የእርማት መስጫዘዴ ለሆንአልቻለም ፡፡ምክንያቱም በምጋቤ ምላሹ ወቅት ለተወሰኑ ስህተቶች ብቻ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው፡፡እንደ ዋና ችግር ተደርጎ ሳይወሰዱ ምጋቤ ምላሽ ያልተሰጣቸው ስለሚዘለሉ በተማሪዎች በኩል ትክክል እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ ፡፡ስለዚህ የቋንቋመምህራን በእርማት ሂደት ምጋቤ ምላሹ የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች በማስገንዘብ የታለፉ ስህተቶች እንደሚገኙና የተሳሳተ የቋንቋአጠቃቀም እንዳይጎለብት በማሳወቅ የተማሪዎችን የግንዛቤ አቅጣጫ ማስፋት ይገባቸዋል (Lalande 1982)

እነዚህ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች በተማሪዎች የጽሁፍ ወረቀት ላይ በሁለት አይነት መንገድ ሰፍረው ሊገኙ ይችላሉ (Keh 1990)::እነሱም በተማሪዎች ጽሁፍ ግራና ቀኝ ባሉት ክፍት ቦታዎች የሚሰጠው ሕዳጋዊ ምጋቤ ምላሽ (Marginal Feedback) ናቸው፡፡በተማሪዎች ጽሁፍ ግራና ቀኝ ባሉት ክፍት ቦታዎች የሚሰጠው ሕዳጋዊ ምጋቤ ምላሽ በጽሁፍ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ መስመር ላይ የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ግልጽና አጭር ነው፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች ስህተታቸውን በፍጥነትና በቀላሉ ለመረዳት ያስችላቸዋል ነገር ግን የጽሁፉን ጥቃቅን ስህተት እንጂ አጠቃላይ የሆነውን እርማት አያሳይም ፡፡

የማጠቃለያ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ መንገድ ግን በጽሁፉ መጨረሻ የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎች የፈጸሙትን አጠቃላይ ስህተት በመጠቆም ጽሁፉን ለማዳበር የሚያግዙ አስተያየቶችን በጽሁፉ መጨረሻ ያመለክታል፡፡ሆኖም ይህ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ መንገድ ለተማሪዎች ግራ የሚያጋባ ነው ፡፡ምክንያቱም በፈጸሙት በእያንዳንዱ ስህተት ዙሪያ ጥቆማ አያካሂድም፡፡ስለዚህ ብቻውን መሰጠቱ ውጤት አልባ ሊያደርገው ስለሚችል ሕዳጋዊ ምጋቤ ምላሽና ማጠቃለያ ምጋቤ ምላሽን በተመጣጠነ ሁኔታ እየተጣመሩ ቢሰጡ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

### 2.1.7 የምጋቤ ምላሽ ባህሪያት

ምጋቤ ምላሽ የተለያዩ ነገሮችን መሰረት በማድረግ እና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለያየ መልኩ Colle and Chan (1994) ሲፈረጁ ይስተዋላል፡፡ለምሳሌ ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ይዘታዊና ቅርጻዊ ምጋቤ ምላሽ ፤አዎንታዊና አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ወዘተ በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ይሁን እንጂ በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ለመዳሰስ የሚሞከረው

አወንታዊና አሉታዊ የምጋቤ ምላሽ ባህሪያቶችን ነው፡፡በCohen.A.D.and Cavalcantl(1990) እና Leki (1990) አገላለጽ የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ለማዳበር የሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ ወደፊት ጠንክረው እንዲሰሩ ተስፋ የሚሰጥና ትችት እንዲታይበት የሚያደርጉ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታዎች ዋንኛቹ አወንታዊ (Positive) እና አሉታዊ /Negative/ በመባል የሚታወቁት የተማሪዎችን የመማር ስሜት የማነሳሳት ወይም የማዳከም አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

### 2.1.7.1 አዎንታዊ / Positive/ ባህሪያት

ይህ የምጋቤ ምላሽ ሁኔታ የተማሪዎችን ክንዋኔ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ ወይም ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ለማቅረብ መሞከራቸውን መምህሩ ትክክል ነው ወይም በጣም ጥሩ መልስ ነው በማለት ጥቆማ የሚያደርግበት ሲሆን ለተማሪዎች በሰሩት ስራ ላይ ጠንካራ ጎናቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ነው(Colle and Chan 1994)

Gipps et al(2004) ገለጻ ደግሞ ለተማሪው የሚቀርበው ምጋቤ ምላሽ ውጤታማ እንዲሆን የተማሪውን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል እንዲረዳና ተስፋ አስቆራጭ እንዳይሆን መምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ አወንታዊ መሆን ይኖርበታል በተጨማሪም አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች የትምህርቱን አላማ ለማሳካት በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዙ የሚያደርግ ስለሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማፋጠን ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ፡፡

እንደ Raimes (1983) ገለጻ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ መልካም ነገር ከተገኘ መጥቀስና ማድነቅ ለመምህሩ ስህተቶችን ለማረም መንገዱን ያቃልልለታል መምህሩ አድናቆትን ለመስጠት በመጀመሪያ የተማሪውን ጽሁፍ በሚገባ ማንበብ ይጠበቅበታል፡፡ከሀሳብ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ስርአተ ነጥብ አመራረጥና አጠቃቀም ድረስ በመውረድ እየተከተለው መሆኑን ከተገለጸለት በቀጣይ ስራ ጠንካራ ጎኑን እንዲከተል ያበረታታዋል ፡፡

በሌላ በኩል አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ በመምህሩ ላይ የስራጫናን አይፈጥርም፡፡ስለዚህመምህራን ከስራ ብዛት የተነሳ እንዲሁም በተማሪዎች ለመወደድ ሲሉ የሚሰጧቸው ምጋቤ ምላሾች አዎንታዊ ወይም ጠንካራ ጎናቸውን ብቻ የሚያንጸባርቅ ከሆነ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ሊያጎለብት አይችልም፡፡በመሆኑም ይህን ሁኔታ መምህራን በመገንዘብ የተማሪዎችን ደካማ ጎኖች የሚያሳዩ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት

አስፈላጊ መሆኑን ማጤንይገባቸዋል፡፡መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ጥሩ በጣም ጥሩ ደህናና የመሳሰሉትን አዎንታዊነት ያላቸውን ቃላት መጠቀማቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ስለዚህ እንደዚህ አንደዚህ አይነት መልሶችን በተናጥል ከመሰጠት ይልቅ ስህተቶቻቸውን ሊያስተካክሉላቸውሊጠቁማቸው ከሚችሉ ምጋቤ ምላሾች ጋር በማጣመር ቢሰጡ ውጤታማ መሆን ይችላሉ (Byrne 1988)::

በአጠቃላይ አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የአመለካከት ለውጥ ከማምጣቱም ባሻገር የመማር ተነሳሽነትን ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ መምህራን ይህን አይነት ምጋቤ ምላሽ ቢጠቀሙበት በተማሪዎቻቸው ላይ የሚታየውን የመጻፍ ክሂል ችግር ሊቀረፍ ይችላል፡፡

2.1.7.2 **አሉታዊ** (Negative) **ባህሪያት**

አሉታዊየምጋቤ ምላሽ ባህሪያት በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ለሚሰሯቸው ለተለያዩ ስህተቶች ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ወይም ይህን አይነት ስህተት መስራትእንደሌለባቸው ለማሳሰብ ወይም በጥቃቅን ጉድለት ለሰሩት የጽሁፍ ስህተትእንደማስጠንቀቂያ ፊትለፊት የሚሰጥ ነው (Leki 1997;Colleand Chan 1994)::

አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ የጽሁፍ ስራው ትክክል አለመሆኑን በሚጠቁም መልኩ ቀለል ባለ ሁኔታ መገለጽ አለበት ፡፤አለበለዚያ ተማሪዎች ለጻፉት ነገር የሚሰጣቸውን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ትችታዊ አድርገው ስለሚቆጥሩ አስተያየቶቹ ምን እንደሚሉ በወጉ ምን እንደሚል ስለሚያነቡት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡በተጨማሪም አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ላይ ሊደርስየሚችለውን አሉታዊ ለውጥ ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት የመምህራንን ብቃት የሚጠይቅ ነው ፡፡በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንዳይጎዳ ስሜታቸውን በማገናዘብ አግባብነት ያለው አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ሊሰጧቸው ይገባዋል ፡፡ይህ ከሆነ ተማሪዎቹ ደካማ ጎናቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ በመረዳት ማስተካከል ይችላሉ(Colle and Chan 1994;225)::

Anderson and Faust (1975) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ደግሞ በአሉታዊ ( Negative)፡ምጋቤ ምላሽ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የጽህፈት ክሂል ችሎታቸውን ያዳብራሉ ፡፡ሆኖም በተማሪዎች በኩል የአሉታዊ (Negative) ምጋቤ ምላሽ ተቀባይነቱ በጣም አነስተኛ ስለሆነ መምህራን አስፈላጊ የሆነ አወንታዊ (Positive) ምጋቤ ምላሽ

በመሰንዘር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ስንረዳው በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በተገቢው ሁኔታ ሀሳባቸውንና አካባቢያቸውን አቀነባብረው እንዲጽፉ እንዲሁም ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል የሚረዳቸው የመምህራን ተገቢ የሆነ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ መኖሩ ተማሪዎቹ ስህተታቸውን እንዳይደግሙ ይጠቅማቸዋል፡፡

## 2.1.8 የውጤታማ ምጋቤ ምላሽ ባህሪያት

ለተማሪዎች ጽሁፍ የሚሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ ውጤታማ ነው ለማለት የራሱ መለያ ባህሪ እንዳለው ምሁራን ይገልጻሉ ፡፡እንደ (Colle and Chan 1994) አመለካከት ደግሞ የውጤታማ ምጋቤ ምላሽ ባህሪዎችን በሚከተለው መልኩ አስፍረዋቸዋል፡-

-መምህሩ የምጋቤ ምላሾችን አይነትና ብዛት ከተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ፤ፍላጎትና እድሜ ጋር በማጣጣም በመርሀ ትምህርቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ሳይሆን ውስን በሆነ ነገር ላይ ያነጣጠረ ግልጽነት ከጎደለው ይልቅ ግልጥነት ባለው ላይ ምጋቤ ምላሽ መቅረብ ብቻ በተማሪዎች ጽሁፍ በሚታዩ ስህተቶች ወይም ጠንካራ ጎኖች ላይ በሚሰጡ ምጋቤ ምላሾች የቋንቋ መምህራን ድርሻ የላቀ ቢሆንም ሁልጊዜም ምጋቤ ምላሹ በእነሱ ብቻ መሰጠቱ ውጤታማ ሊያደርገው አይችልም ፡፡ስለዚህ በተማሪዎች መካከል የርስ በርስ (ቢጤ) እርማት እንዲያደርጉ እድሉን በማመቻቸት የመማር ማስተማሩን አቅጣጫን ማቀላቀል ሲቻል ፤ምጋቤ ምላሹ በተማሪዎች ልምምድ ላይ ትኩረት ለማድረግ የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውን በማሻሻል በኩል ተገቢ የሆኑትን በማበረታታት ወይም የታዩትን ስህተቶች ጥቆማ የሚያደርግ እንጅ ስህተት ለምን ተገኘ ተብሎ አላስፈላጊ እርምጃ ውስጥ የማይገባ ሲሆን፤

ምጋቤ ምላሹ በመርኃ ግብሩ መሰረት የታቀዱትን ልምምዶች በክንውን ላይ እያሉ የሚሰጥ ሲሆን በተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ ላይ የሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ የሚገለጽበት ሁኔታ ጽኑነትና ተቀባይነት ያለው የአስተራረም ስልት ያለው ሆኖ ሲገኝ ፤ማለትም ምጋቤ ምላሽ መሰጠት ያለበት ስህተቶችን ሳይዘል ጥቆማ ሰጥቶ የሚሄድ ወይም በአንድ የጽሁፍ መልመጃ ማበረታታት ወይም የተገኙትን ስህተቶች ምጋቤምላሽ የተሰጡትን

ነጥብ በሌላው ተማሪ ጽሁፍ መልመጃ ላይ ይህንኑ ሳይለወጥ በወጥነት ከተሰጠ፤የሚሉት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ምጋቤ ምላሽ አስፈላጊየሚሆነው ተማሪዎች የሚጽፉት ድርሰት የተዋጣለት እንዲሆንና በሚገባ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ በተደጋጋሚ ጽሁፍ እንዲጽፉ በማድረግና መምህራን ጽሁፉን በማየት አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ስህተቶቻቸውን እያረሙእንዲሰሩ በአዎንታዊ የምጋቤ ምላሽ ባህሪ በመጠቀም እንዲሁም አጠናካሪና አስተካካይ የምጋቤ ምላሽ አይነት ተጠቅመው ጥቆማ በመስጠት የመጻፍ ችሎታቸውን ማሻሻል ተችሏል፡፡

## 2.2 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

ይህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች የሚጠቀሱበት ነው፡፡ይህውም የጥናቱን ርእስ ፤ዐላማ፡ አጠናን ዘዴና የተደረሰበትን ውጤት በመግለጽ፡ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ልዩነት የሚያመላክቱ ነጥቦችን ይገልጻል፡፡

ግርማ(1990) “በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብር ስልት /Intreractive Approach/ ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት”በሚል ርእስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ አላማም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ክሂልን ማዳበር ያስችል እንደሆን ለመፈተሽበገላጭ የጥናት ዘዴ በአንድ ቡድን የታቀፉ ተጠኝዎች ላይ ማጥናት ነው፡፡ተጠኝዎቹም የተመረጡት በአመች ናሙና ሲሆን በሀድያ ዞን የካቲት 25/67 ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ1990 በ10ኛ ‘ E ‘ ክፍል የሚማሩ የአማርኛ ቋንቋ አፊ ፊትና ኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች ናቸው ፡፡የመረጃ መሰብበ.ያዘዴው ምልከታ ፤ የጽሁፍ መጠይቅና መስተጋብራዊ ስልት ነው ፡፡በጥናቱ የተገኘው ውጤት መስተጋብራዊ ስልት በድርሰት ማስተማሪያ ዘዴነት በተግባር ላይ ቢውል በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህሩ ለተማሪዎቹ እንደሚፈልጉት ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስችል የሚረዳ መሆኑን አሳይቷል፡፡

አስካለ (2001) የጥናቱ ርእስ “ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች በመምህራን የሚሰጡ ምላሾች የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያላቸው ተጽእኖ” የሚል ሲሆን የጥናቱ አላማም የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ምጋቤ ምላሽ

የመጻፍ ችሎታቸውን በማዳበር በኩል የሚያመጣውን ተጽእኖ መፈተሽ ነው ፡፡ተጠኘኝዎቹ በባህርዳር በመራዊ መሰናዶ ተምህርት ቤት በ2001 ዐ.ም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና የተመረጡ ሲሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም ሰነድ ፍተሻ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ በመጠቀም ሲሆን የአጠናን ዘዴውም ገላጭ ቅኝታዊ የምርምር ስልት በመጠቀም በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት “ Repeated Measures Sample t-test”ስሌት ተጠቅመዋል ፡፡ጥናቱም የደረሰበት ውጤት በመምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የጽሀፈት ችሎታ እንደሚቀንስ የሚያመጣው ተጽእኖ ከፍተኛ እንደሆነና ተማሪዎች ከምጋቤ ምላሽበፊትና በኋላ በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል አለመታየቱን ያመለክታል ፡፡

እነዚህ ሁለቱ ጥናቶች የሚያመሳስላቸው በተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ዙሪያ ሆኖ በገላጭየአጠናን ዘዴ መጠናቱ ነው ፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ያለውቸው ልዩነት ደግሞ የመጀመሪያው አፈፊትና ኢ-አፈፊት ባንድ ላይ ሆነው መስተጋብራዊ ስልት ተግባራዊ ቢሆን በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህሩ ለተማሪዎቹ እንደሚፈልጉት ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስችለው ማሳየቱ ይህ ጥናት የሚካሄደው ደግሞ በአፈ ፊት መሆኑ ነው፤፤ በሁለተኛው ጥናት በመምህራንየሚሰጡ ምጋቤ ምላሾች በተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ላይ ምንምለውጥ አለማሳየቱን የሚያመለክት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በመምህራን የሚሰጡ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች የተማሪዎችን የድርሰት መጻፍ ችሎታ እንደሚያዳብር ጥናቱ አመልክቷል፡፡

እታለማሁ (2006) “የ9ነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የመጻፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ፍተሻ” የሚል ነው ፡፡›› የጥናቱ አላማም የቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ የሚሰጧቸውን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መፈተሽ ነው ፡፡ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የካቲት 23 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመች ናሙና አመራረጥ በመምረጥ ተካሂዷል ፡፡የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም የተማሪዎችጽሁፎች ፤የጽሁፍ መጠይቅናቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡በጥናቱ የተገኘው ውጤት ደግሞ መምህራን ገምጋሚ ምጋቤ ምላሽን አዘውትረው እንደሚጠቀሙና በዋናነት ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን ተጠቅመው የተማሪዎችን ጽሁፍ እንደሚያሻሽሉ የትንተናው ውጤት አሳይቷል፡፡

እንዳለ (1992) የጥናቱ ርእስ “ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና” በሚል ርእስ የቀረበ ሲሆን አላማውም ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን ሚና በሳይንሳዊ ዘዴ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱን ለማከናወን ተጠኝ ቡድኖችን በአጋጣሚ ለመምረጥ ቅድመ ልምምድ (Pretest ) እና ድህረ ልምምድ (Post test) ፈተናዎች ይሰጣሉ የመረጃ መተንተኛ ዘዴውም ስታስቲካዊ ሲሆን ትምህርት ቤቱም በምክንያታዊ ናሙና አመራረጥ የተመረጠ ነው፡፡ጥናቱም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የ11ኛ የክፍል ተማሪዎችን በ18 መማሪያ ክፍል 2ቱ በእጣ ናሙና የተለዩ ሲሆን በእጣው መሰረት አንዱ የሙከራ (Expermental group) ሌላው ጥብቅ (Controlled Group) ቡድን በማለት በአጥኝው ተመድቧል ፡፡መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው በጽሁፍ መጠይቅ ፤በቃለ መጠይቅ ና በምልከታ ሆኖ የተገኘው ውጤትም ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ ችሎታ እንደሚሻሻል በጥናቱ ተረጋግጧል

ሁለቱ ጥናቶች የሚያመሳስላቸው በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ መሻሻል ላይ መምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ላይ ሲሆን ፡፡ ልዩነቱ ደግሞ የምርምር ዘዴው እታለማሁ (2006)የተጠቀሙት አይነታዊናመጠናዊ ሲሆን እንዳለ (1992)ደግሞ በሳይንሳዊ ዘዴ ተጠቅመው የሙከራ ክፍልና ጥብቅ ክፍል በማለት ንጽጽራዊ ዘዴን መጠቀማቸውን ሲያሳይ የተጠኝ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲሁም የተጠናበት አመተ ምህረት የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ ጥናት የሚለየው መምህራን ገምጋሚ ምጋቤ ምላሽ በመጠቀም የተማሪዎች የድርሰት መጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ከአስተካካይ እና አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ የተሸለ አይሆንም ስለዚህ ይህ ጥናት አስተካካይና አጠናካሪ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት የተማሪዎችን የድርሰት ጽሁፍ እንደሚያሻሽል አሳይቷል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

### የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ አላማውን ከግብ ለማድረስ አጥኝዋ የተጠቀመችበት የአጠናን ዘዴ መጠናዊ ላይ የተመሰረተ ከፊል ሙከራዊ ነው፡፡ለጥናቱም የሚያስፈልጉ መረጃዎች በድርሰት ፈተና፣በጽሁፍ መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ተሰብስቧል፡፡

### 3.1የናሙናአመራረጥ

### 3.1.1 የጥናቱ አካላይ

ይህጥናት በአማራ ክልልበሰሜንሸዋዞንበመንዝላሎምድርወረዳ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመንዝላሎ ምድር ወረዳ ሁለት 2ኛደረጃትምህርትቤቶች ሲኖሩ በወገሬ 750 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጦል 250 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡በአጠቃላይ1000የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ጥናቱ የሚካሄደው በወገሬሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡ ይህውም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በመያዙ ለጥናቱ ተተኳሪ ሆኖ በአመቺናሙናአመራረጥ ተመርጧል፡፡ ተማሪዎቹ የሚማሩበትክፍል ደግሞእጣበማዉጣትየንሞናዘዴ ተመርጠዋል፡፡

### 3.1.2የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመጻፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ትንተና ነው፡፡ስለዚህ በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ በሚገኙሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የወገሬ ትምህርት ቤት ለጥናቱ ተተኳሪ ሆኗል፡፡ይህ ትምህርት ቤት የተወሰደው በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጦ ነው፡፡

### 3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በተጠኝነት የተመረጡት በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ በወገሬ 2ኛ ደረጃ በ2011 ዓ.ምየትምህርት ዘመን በ9ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህ የተመረጠበት ዋና ምክንያትየ9ኛክፍል ተማሪዎች ከታች ጀምረው ድርሰት መጻፍ ቢለማመዱ መሰረት በመያዝ ለላይኛው የክፍል ደረጃቸው ቀና ሆኖ የውስጥ ሀሳባቸውን፤ የሀገራቸውን ባህልና ታሪክ ለመጻፍ እንዲያስችላቸው በማሰብ ነው፡፡እንዲሁም በአማረኛ ቋንቋ በትምህርት ቤት ውስጥ የድርሰት መጻፍ ልምምድ ማድረጉ በሌሎቹም የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ጥናቱ እንደሚያገለግል ስለታመነ ነው፡፡

### 3.1.4 የተጠኝ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በወገሬ አጠቃላይሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ለጥናቱርእስትኩረትበመስጠት የጽህፈት ስራይከናወንበታል፡፡ አጥኝዋ ከሶስት የአማርኛ ቋንቋመምህራን ጋር በመሆን በትምህርት ቤት ውስጥ ካሉት 15 የ9ኛ ክፍልመማሪያ ምድቦች መካከል እጣ ጠቅልሎ ናሙና በመምረጥ ዘዴበመጠቀም ሁለት ምድቦችን ወስዳ ከሁለቱ መካከል እጣበማውጣት አንዱ የሙከራ ቡድን ሌላው አንዱ ምድብ ደግሞ የጥብቅ ቡድን ሆኗል፡፡ይህም የሆነው ተማሪዎቹ የግል እንጅ የቡድን ችሎታ ልዩነት እንደሌላቸው ከትምህርት ቤቱ ሱፐርቫይዘር ጋር በአመዘጋገባቸው ሁኔታ እና በክፍል አደላደላቸው ዙሪያ ተመጣጣኝ እንደሆኑ አጥኝዋ ባገኘችው መረጃ በማረጋገጥ ነው፡፡ ሁለቱ ክፍሎች 100 ተማሪዎች የተመደቡ ሲሆን ከጠቅላላው በወረዳው ካሉ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ከ1000 ተማሪዎች ውስጥአስሩን ፐርሰንት የያዙ ናቸው፡፡ከነዚህ መቶ ተማሪዎች ውስጥ 10 ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው በተለያየ ችግር ያቋረጡ ሲሆኑ 8ቱ ደግሞ በተከታታይ በድርሰት መጻፉ ፈተና ወቅት ባለመገኘታቸው ምክንያት በጥናቱ ውስጥ አልታቀፉም በጥናቱ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሲከታተሉ የቆዩ ተማሪዎች ከሙከራ ቡድን 41 ከጥብቅ ቡድን 41 በአጠቃላይ 82 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ናቸው፡፡

### 3.1.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በዋናነት መሰረት አድርጎ የተነሳው የመምህራን ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታ በማዳበር ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ላይ ያነጣጠረ ሲሆን

ትኩረቱም በመምህራን  ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ላይ ይሆናል፡፡በዚህም በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በወገሬ ትምህርት ቤትና በጦል ትምህርት ቤት 6 የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ በጠቅላይ ናሙና ዘዴ (Comprehensive Sampling) መሰረት በጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ከ6ቱ መምህራን መካከል 2ቱ ወንዶች ሲሆኑ የቀሩት ሴቶች ናቸው ሁሉም የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸውና ከሶስት አመት በላይ አገልግሎት ያላቸው ናቸው፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የጥናቱን አላማ ለማሳካት አግባብነት አላቸው ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሶስት የተለያዩ መንገዶች ናቸው ፡፡የመጀመሪያው የድርሰት ፈተና ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች የድርሰት መጻፍ ልምምድ ከማከናወናቸው በፊት ወይም ምጋቤ ምላሽ ከማግኘታቸው በፊትና ካከናወኑ በኋላ ወይም ምጋቤ ምላሽ ካገኙ በኋላ ያመጡትን የድርሰት መጻፍ ችሎታ ለውጥ ለመመዘን የሚያገለግል ነው፡፡ ይህውም ትምህርት ቤቱ ካሉት 15 የ9ኛ መማሪያ ክፍል ምድቦች መካከል ሁለት ምድቦች በእጣ ተመድበዋል፡፡ በእጣው መሰረት አንዱ(9ኛኤ) 41 ተማሪዎች የሙከራ ቡድን ሌላው (9ኛቢ)41 ተማሪዎች የጥብቅ ቡድን በሚል ተመድቧል፡፡የሙከራ ቡድን አባላት በየ15 ቀን ለአራት ጊዜ በተከታታይ ለሁለት ወር በትምህርት ቤቱ ባሉት አማርኛ መምህራን አማካይነት በተመረጠው "የእናት ፍቅር" በሚለው ርእስ ድርሰት በማጻፍና ሂደታዊ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት የድርሰት መጻፍ ልምምድ እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡ጥብቅ ቡድኑም በተመሳሳይ የጽህፈት ተግባር ሲፈጽም ቆይቷል፡፡ነገር ግን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አልተሰጡም፡፡ለመረጃነት የሚያገለግሉት የድርሰት ፈተናዎች የሙከራ ቡድኑና የጥብቅ ቡድኑ የቅድመ ድርሰት መጻፍ ፈተና እንዲሁም የሁለቱም ቡድኖች  የድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና አማካይ ውጤት ተወስደዋል፡፡

ሁለተኛው ቃለ መጠይቅ ሲሆን ይህውም ከመምህራን ጋር በምጋቤ ምላሽአሰጣጥና በተማሪዎች የድርሰት አጻጻፍ ዙሪያ በሚያመጣው ለውጥ ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት የሚፈትሽ ነው፡፡ሌላው ከትምህርት ቤቱ ሱፐርቫይዘር ጋር የሚደረግ ቃለምልልስ በትምህርት ቤቱ ያሉ የተማሪዎች ብዛት ፤እንዲሁምየ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት

የአመዘጋገባቸውን ሁኔታና ከችሎታ አንጻር የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ተመጣጣኝነት ያረጋገጠና የአመዳደብ ሁኔታን በተመለከተ ዳሷል፡፤

ሶስተኛው ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ ነው በጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በመምህራን ምጋቤ ምላሽአሰጣጥ ዙሪያየጥናቱን አላማ መሰረት ያደረጉ 12 ጥያቄዎች አማራጭ የተሰጣቸው ናቸው፡፡አማራጫቸውም በጣም እስማማለሁ 4፣እስማማለሁ 3፣አልስማማም 2 እና በችራሽ አልስማማም1 ናቸው፡፡ተማሪዎቹ ካነበቡ በኋላ ከተሰጡት አማራጮች" X "ምልክት በመጠቀም ሀሳባቸውን ገልጸዋል፡፡በተጨማሪ ለሶስት ክፍት ጥያቄዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ ገልጸዋል፡፡

## 3.2.1 የድርሰት መጻፍ ፈተና

### ሀ.ቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና

የቅድመ ልምምድ ፈተና የተሰጠው ተጠኝዎች የድርሰት መጻፍ ልምምድ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ያላቸውን የድርሰት መጻፍ ችሎታ ለመለካት እና በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል የችሎታ ተመጣጣኝነት መኖሩን ከትምህርት ቤቱ ሱፐርቫይዘር የተማሪዎችን የአመዘጋገብና የክፍል አደላደል ሁኔታ እንዲሁም የጾታ ተመጣጣኝነት በተገኘው መረጃ መረጋገጡ ጥናቱ አስተማማኝ እንዲሆን መሰረት ሆኗል ፡፡ ይህን በአባሪ "መ"ላይ ይመልከቱ፡፡ስለሆነም ቅድመ ድርሰት መጻፍ ልምምድ ፈተና መስጠት አስፈላጊ ሆኗልለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ አራት ርዕሶች በአጥኝዋ ተዘጋጅተዋል እነሱም "ከትምህርት ቤት መቅረት"፣"ትምህርት ቤት"፡" የጥናት መርሃ ግብር"እና"የእናት ፍቅር"ሲሆኑርዕሶቹም ለሶስት የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቀርበውአስተያየት ሰጥተውባቸው"የእናት ፍቅር"የሚለውን ርእስ መርጠው ተጠኝ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ድርሰት እንዲጽፉ ከታመነበት በኋላ ወደ ስራውተገባ፡፡በአንድ ርእስ ለ4 ጊዜ በተደጋጋሚ ድርሰት እንዲጽፉ የተደረገው shih (1989) እንደገለጹት ለተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ በመምህራን የተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ የተዋጣለት የሚሆነው የጽሁፉን ይዘት መሰረት ካደረገ ነው ፡፡ይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ ማለት ደግሞ የተማሪዎች የጽሁፍ ፈተና ከሃሳብ አንድነት፣አደረጃጀት ፣ጥልቀትና ፍች መሰረት ያደረገ መሆኑን እንደገለጹት ተማሪዎቹም በአንድ ርእስ ላይ በእነዚህ ዙሪያ የተሰጣቸውን

ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚገባ ለይተው ካወቁ ለሌላው ጽሁፋቸው መሰረት ይሆናቸዋል ተብሎ ስለታሰበ ተግባራዊተደርጓል፡፡

ፈተናው መደበኛውን የአማርኛ ክፍለጊዜ በመከተል ተከናውኗል ለፈተናው መስሪያ የሚያገለግል በሁለቱም ጎኑ ህዳግ ያለው ባለመስመር ወረቀት ታድለው በወረቀቱ ራስጌ ክፍላቸውን፣ምድባቸውን፣ቁጥራቸውን እና ጾታቸውን እንዲጽፉ እንዲሁም ጽሁፋቸው ከአንድ ገጽእንዳይበልጥ ተነግሯቸው የተመረጠው ርእስተሰቷቸው በ40 ደቂቃ ውስጥ ጽፈው እንዲጨርሱተገልጾላቸው ፈተናው በሁለት መምህራን የተከናወነ ሲሆን የሙከራ ቡድኑን በአንደኛው መምህር የጥብቅ ቡድኑን በአጥኝዋ ተካሄዷል፡፡

ተጠኝ ተማሪዎችም በየ15 ቀን ለ4ጊዜ በተከታታይ ለሁለት ወር በተመረጠው ርእስ የድርሰት መጻፍ ፈተናው ተከናውኖ በትምህርት ቤት ያሉ ሶስት የአማርኛ መምህራን ታርሚል በአራሚዎቹ መካካል የሚኖረውን ልዩነት ለማጥበብ እና ተመሳሳይ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የ (heaton 1988) ሀሳቦች በመውሰድ የድርሰት አስተራረም መመሪያ ተባዝቶ ለእያንዳንዱ አራሚ ተሰጥቶ ይህ የማረሚያ ቅጽ ባለ 5 ክፍል ሆኖ (ይዘት 30% ፣አደረጃጀት 20%፣የቋንቋ አጠቃቀም 25%፣ ቃላት 20%፣ እና ቅርጽ 5% አጠቃላይ ከ100ፐርሰንት መመዘኛ ሆኗል ይህ በአባሪ ሀ ላይ ይገኛል አጠቃላይ ከሙቶ የተያዘበት ምክንያት ውጤታቸውን በፐርሰንት ለመግለጽና በአማካይ ቁጥር ለማስቀመጥ ሲሆን ለእያንዳንዱ የተሰጠው ውጤት ደግሞ ለአንድ ጽሁፍ አስፈላጊነታቸውን በማዛመድ ነው፡፡ይህን በዝርዝር ለማየት በክለሳ ድርሳናት ላይ 2.1.4.1 የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት አቅጣጫ ስር ተገልጿል፡፡በተጨማሪ በአባሪ ሀ ላይይገኛል፡፡

## ለ.ድህረ ድርሰት ልምምድ ፈተና

ከሁለት ወራት የድርሰት መጻፍ ልምምድ በኋላ ተጠኝዎች የሙከራ ቡድኑ አባላት በድርሰት መጻፍ ችሎታቸው ላይ ለውጥ አሳይተው እንደሆነ ለመመዘን ለውጡንም ከጥብቅ ቡድን አባላት ውጤት ጋር በማነጻጸር የተሰጠውንም ምጋቤ ምላሽ ጠቀሜታ ለማየት ይቻል ዘንድየድርሰት መጻፍ ፈተና ተሰጥቷል ቅድመ ልምምድ የድርሰት ፈተና በጻፉበት ርዕስ መልሰው እንዲጽፉበት ማድረግ የችሎታ ለውጦችን በማስተያየት ለመዳኘት፤ የተሸለ ድርሰት መጻፋቸውንና ስህተታቸውን አውቀው ተግባራዊ

ማድረጋቸውንም ለማየት እንዲያስችል የአማርኛ መምህራን በመረጡት ርእስ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

የድህረ ድርሰት ፈተና እንደ ቅድመ ድርሰት ፈተና በተመሳሳይ የማረሚያ መስፈርት ሶስት መምህራኖች አርመው የሰጡትን ውጤት አማካዩን በመያዝ ከመቶ ከተደመረ በኋላ አጠካላይ አማካይ በማስላት የሙከራ ቡድኑ 81.7 ሲሆን የጥብቅ ቡድኑ ደግሞ 67.1 ሆናል፡፡

የሙከራ ቡድኑየቅድመ ድርሰትና የድህረ ድርሰት ፈተና ውጤት ልይይት 0.000*በመሆኑ የቲ-ቴስት ዋጋው ከ0.5 በማነሱ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡ልዩነት የተፈጠረውም መምህራን በሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ የተሻሻለ መሆኑን ነው፡፡

የጥብቅ ቡድኑ የቅድመ ድርሰት ፈተና ከድህረ ድርሰት ፈተና ጋር ሲነጻጸር የሚያሳየው ልዩነት .051በመሆኑ እና ይህ ደግሞ ከቲ-ቴስት ዋጋ ከ0.5 በላይ በመሆኑ ልዩነት እንደሌለ ያሳያል፡፡ይህ የሚያመላክተው ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ባለማግኘታቸውየተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደፈጠረባቸው ያመላክታል፡፡

### 3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የድርሰት መጻፍ ልምምዱ ወይም የጽህፈትትምህርት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለሚገኝበት ሁኔታ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ እናየጥናቱን ጥያቄዎችበተጠኝ ተማሪዎች በ9ኛ ኤና9ኛቢ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችየተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

ተጠኝዎቹ ከ2ወራት ድርሰት የመጻፍ ልምምዳቸው በፊትና በልምምዱ ወቅት ከጽህፈት ተግባራትና ከጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መቀበል ጋር ስለነበራቸው ሁኔታ ያላቸውን አስተያየት ለመረዳት የሚጠቅም መጠይቅ ነው፡፡

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ክፍል አንድ፡ጾታ፤እድሜ፤የአፍ መፍቻ ቋንቋ ይጠይቃል፡፡ክፍል ሁለት 12 ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ተማሪዎቹ በእስካሁን የትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት ስለአካሄዱት የድርሰት መጻፍ ልምምድናየእርማት ሁኔታ ተማሪዎች

ለሚሰጧቸው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያላቸውን አስተያየትና የአቀባበል ሁኔታ ይበልጥ ንቁ ምላሽ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አይነት በሂደታዊ ድርሰት አጻጻፍ ይዘትና ቅርጽነክ አስተያየቶች የተሻለ ውጤት የሚኖራቸው በየትኛው ረቂቅ ደረጃ ሲሰጡ እንደሆነ የተማሪዎችን የድርሰት መጻፍ ስሜት የሚቀሰቅሱ ወይም የሚያቀዘቅዙ የጽህፈት መምህራን አስተያየቶች ስለመኖራቸው የጽሁፋዊ አስተያየት ሰጭመምህራን ሚና እንዴት እንደሚገነዘቡት የሚያሳዩ ጥያቄዎች ይሆናሉ፡፡ጥያቄዎቹየተዘጋጁትምአማራጮችን በመስጠት ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ነው፡፡በመጨረሻም ክፍት ጨራሽ ጥያቄዎችን በማከል የጽሁፍ አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

### 3.2.3 ቃለ መጠይቅ

በሁለተኛነት የቀረበው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ሱፐርቫይዘርና ለመምህራን የቀረበ ሲሆን አላማውም ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የጽሁፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውን አስተዋጽኦየሚፈትሽ ነው፡፡ይህን አስመልክቶ ከሱፐርቫይዘር ጋር የተደረገው መጠይቅ አላማው ለቅድመ ድርሰት መጻፍ ፈተና በተማሪዎች መካከል የእውቀት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ እንዲሁም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ለማወቅ የቀረቡ ናቸው፡፡ይህን (በአባሪ- መ)ይመልከቱ፡፡ ከመምህር ጋር የተደረጉ ቃለ መጠይቆች በአጥኝዋ ተዘጋጅተው ለድርሰት ፈተና እርማት በሰጡት መምህራን እና በአማካሪ ከተገመገሙ በኋላ አስፈላጊውን ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡የጥያቄዎቹም ብዛት ስምንት ናቸው፡፡ እነሱም ፡-ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት በመምህራን የሚሰጡ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች አላማ ምን እንደሆነ፣የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ ድርሰቶች ላይ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ስለመስጠታቸው፣በተማሪዎች ድርሰቶች ለይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ፣ከሚሰጡት ምጋቤ ምላሾች መካከል ለተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ ይበልጥ የሚረዳ መኖሩን፣ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት መጻፍ አወንታዊ ገጽታ ያለው መሆኑን፣ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ አስተዋጽኦ መኖሩን፣ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ከሚፈጸሙ የስህተት አይነትውስጥ የትኛው ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያርሙ እና ተማሪዎች ለሚሰጣቸው ጽሁፋዊ

ምጋቤ ምላሾች እንዴት አንደሚቀበሉት ምላሽ የተሰጡባቸው ናቸው፡፡ ይህንን (በአባሪ ሐ ላይ ይመልከቱ)፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን

ይህ ጥናት በምእራፉ የተነሱትን የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ በቅድመና በድህረ ልምምድ ፈተና ወቅት የተገኙ ውጤቶች በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡ ጭብጦች ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ ችሎታ ላይ ለውጥ ማስገኘቱን ለማረጋገጥ ተተንትነዋል፡፡ በተጨማሪም የመምህራን ቃለምልልስ የተጨበጡ ፍሬ ሀሳቦች ለትንታኔው ማበልጸጊያነት ውሏል፡፡

ቅድመ ድርሰት መጻፍ ልምምዱ ፈተና የወሰዱ ተጠኝዎች 82 ናቸው፡፡ድህረ ፈተና የሚወስዱትም ተጠኝዎች እነዚሁ ተጠኝ ተማሪዎች ናቸው በጥናቱ ውጤት ትንታኔ ላይም መዛባት እንዳያስከትል የመጀመሪያውን ወይም ሁለተኛውን ፈተና ያልወሰዱ ተማሪዎች በጥናቱ አልታቀፉም በተጨማሪ የሙከራ ቡድን አባላት 41 የጥብቅ ቡድን አባላት 41 ናቸው፡፡

መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው እርማቶች በመጻፍ ችሎታቸው ላይ የሚያመጡትን ለውጥ ለማወቅ ደግሞ የእያንዳንዱን ተማሪ የድርሰት ፈተና የሚያርሙ መምህራኖች ተቀራራቢ ውጤት እንዲሰጡ በሚከተሉት ምድቦች ዝርዝርነጥብ በማስቀመጥ አራሚዎቹ በተቀመጠላቸው ነጥብ ውስጥ ሀሳባቸውን እንዲያስቀምጡተደርጓል ይህም በአባሪ ሀ ተገልጿል፡፡ምድቦቹም ይዘት 30%፣አደረጃጀት 20%፣ የቋንቋአጠቃቀም 25%፣ ቃላት 20%እናቅርጽ 5% በጠቅላላው 100ፐርሰንት ላይ የሚያተኩረውን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ባሉ በ3 የአማርኛቋንቋ መምንራን አራሚዎች የተገኘው የእያንዳንዱ ምድብ የያንዳንዱ ተማሪ ውጤት ተደምሮ ለ3 ተካፍሎ የተገኘውን አማካይ ውጤት ከመቶ ደምሮ የ41 ተማሪ አማካይ ውጤቱ ደምሮ በማካፈል አጠቃላይ የሙከራ ቡድን የቅድመ ድርሰት 68.3 እና የድህረ ድርሰት ውጤት 81.7 መሆኑን በትንተናው አመልክቷል፡፡እንዲሁም የጥብቅ ቡድን የቅድመ ድርሰት መጻፍ ፈተና የተገኘው ውጤት 70.2ሲሆን የድህረ ድርሰት ውጤት ደግሞ 67.1 ይህንን ውጤት ትንታኘው ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተና ማብራሪያ

## 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

ጥናቱ አላማ አድርጐ የተነሳው የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያለው አስተዋፅኦ መፈተሽ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በድርሰትፈተና በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የድርሰት መፃፍ ችሎታ ያሻሽላልን? የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰቶች ላይ የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ምን ላይ ነው? መምህራን በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ የሚሰጣቸው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች አወንታዊና አሉታዊ ገፅታዎች አሏቸውን?የቋንቋ መምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ረገድ ምን ዘዴ ይጠቀማሉ? ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠትናጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ባለመስጠት መካከል ልዩነት አለ? የሚሉትን የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎችንመሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.1 የድርሰት መፃፍ ፈተና ትንተና

የድርሰት መፃፍ ፈተናው ያተኮረው ተማሪዎች በሚፅፉት ድርሰት ላይ መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያለው አስተዋፅኦ ላይ ነው፡፡ በወገሬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ከ15 መማሪያ ክፍሎች ውስጥ ማለትም ከ750 ተማሪዎች ሁለቱን ክፍል 9ኛ A እና 9ኛ B ክፍልን በእጣ ከተመረጡ በኋላ በእያንዳዱ ክፍል 41 ተማሪዎች ለፈተና የቀረቡ ሲሆን በ9ኛ A እና 9ኛ B ያሉ ተማሪዎች የድርሰት መጻፍ ፈተና ለመፈተን“ማርፈድ ክልክል ነው”፡፡ “የእናት ፍቅር፣“ከትምህርት ቤት መቅረት”እና “የጥናት መርሀ ግብር” የሚሉ ርእሶችን በትምህርት ቤቱ ላሉ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንአንዱን እንዲመርጡ አጥኚዋአቅርባ “የእናት ፍቅር”የሚለው ተመርጦተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፉ ተደርገ፡፡

የሙከራ ቡድን 9ኛኤ የጥብቅ ቡድን9ኛቢናቸው፡፡ የሁለቱንም ክፍሎችየመጀመሪያ ፈተና የተመረጡት ሶስትመምህራን እንዲያርሙ ተደርጐ ለሙከራ ቡድኑ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሲሰጣቸውስህተታቸውን አስተካክለው እንዲፅፉ በማድረግ በተደጋጋሚ በዚህ ርዕሰ

ሲፈተኑ9ኛቢ የጥብቅ ቡድኑ ግን የታረመው ድርሰት ማስተካከያ እርማት በጽሑፍ ሳይመለስላቸው ያገኙትን ውጤት ብቻ በማስቀመጥ በተደጋጋሚ ለ4 ጊዜ በዚሁ ርዕስ ድርሰት መፃፍ እንዲፈተኑ ተደረገ በአንድ ርእስ ለ4 ጊዜ በተደጋጋሚ ድርሰት እንዲጽፉ የተደረገው shih (1989) እንደገለጹት ለተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ በመምህራን የተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ የተዋጣለት የሚሆነው የጽሁፉን ይዘት መሰረት ካደረገ ነው ፡፡ይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ ማለት ደግሞ የተማሪዎች የጽሁፍ ፈተና ከሃሳብ አንድነት፣አደረጃጀት ፣ጥልቀትና ፍች መሰረት ያደረገ መሆኑን እንደገለጹት ተማሪዎቹም በአንድ ርእስ ላይ በእነዚህ ዙሪያ የተሰጣቸውን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚገባ ለይተው ካወቁና ይህንን አስተካክለው ከጻፉ ለሌላው ጽሁፋቸው መሰረት ይሆናቸዋል ተብሎ ስለታሰበ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የቅድመ ድርሰት ፈተና እና የድህረ ድርሰት ፈተና የሶስቱ አራሚዎች አማካይውጤት ተወስዷል፡፡

በአራሚዎቹ መካካል የሚኖረውን ልዩነት ለማጥበብ እና ተመሳሳይ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የ (heaton 1991) ሀሳቦች በመውሰድ የድርሰት አስተራረም መመሪያ ተባዝቶ ለእያንዳንዱ አራሚ ተሰጥቶ ይህ የማረሚያ ቅጽ ባለ 5 ክፍል ሆኖ (ይዘት 30% ፣አደረጃጀት 20%፣የቋንቋ አጠቃቀም 25%፣ ቃላት 20%፣ እና ቅርጽ 5% አጠቃላይ ከ100ፐርሰንት መመዘኛ ሆኗል ይህ በአባሪ ሀ ላይ ይገኛል አጠቃላይ ከመቶ የተያዘበት ምክንያት ውጤታቸውን በፐርሰንት ለመግለጽና በአማካይ ቁጥር ለማስቀመጥ ሲሆን ለእያንዳንዱ የተሰጠው ውጤት ደግሞ ለአንድ ጽሁፍ አስፈላጊነታቸውን በማዛመድ ነው፡፡ይህን በዝርዝር ለማየት በክለሳ ድርሳናት ላይ 2.1.4.1 የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት አቅጣጫ ስር ተገልጿል፡፡በተጨማሪ በአባሪ ሀ ላይ ይገኛል፡፡በመሆኑም ከክለሳ ድርሳናት ስር የቀረቡትን የተለያዩ ንድፈ ሀሣባች መነሻ በማድረግ በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የቅድመ ድርሰት ፈተና እና የድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና ችሎታ ምን እነደሚመስል እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

## ሀ. በተማሪዎችየድርሰት መጻፍ ፈተና የመምህራን ፅህፋዊ ምጋቤ ምላሽ ትንተና

መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጣቸው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማዳበር በኩል ክፍተኛ ጥቅም እንዳለው ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ይህንን ለማወቅ የሚቻለው ደግሞ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሲታይ ነው፡፡ በመሆኑም ክክለሳ ድርሳናት ስር የቀረቡትን የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የቅድመ

ድርሰት ፈተና ጽሑፋዊምጋቤ ምላሾች ተሰጥቶአቸው ስህተታቸውን እያረሙ ድርሰት ደጋግመው የፃፉትን  የቅድመ ድርሰትና  የድህረ ድርሰቱን ለውጥ ማየት እንዲሁም ምጋቤ ምላሽ ሳይሰጣቸው በአንድ አይነት ርዕስ ደጋግመው የፃፉት የቅድመ ድርሰትና የድህረ ድርሰቱ ልዩነት ማረጋገጥና በተጨማሪ /በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የድርሰት መፃፍ ችሎታ የመሻሻል ሁኔታ የታየው በየትኛው እንደሆነ ለመለየት የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት ነጥቦች ይዘት 30%፣ አደረጃጀት 20% ፣ ቃላት 20%፣ የቋንቋ አጠቃቀምና 25% እና ቅርጽ 5% በተመለከተለእያንዳንዱ በስራቸው ነጥብ በመስጠት የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ከመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት አንጻር ተተንትኗል፡፡

ሰንጠረዥ1 በይዘት ላይ ተመስርተው የተሰጡ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላ

| ይዘትን የሚያመላክቱ የትኩረት ነጥቦች 30% | የሙከራ ቡድን | | | | የጥብቅ ቡድን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ፤በደንብ ያተኮረ 26 -30 % | 5 | 12.2 | 27 | 65.8 | 5 | 12.2 | 3 | 7.3 |
| ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት የያዘ በበቂ ደረጃ የቀረበ 21- 25% | 10 | 24.4 | 10 | 24.4 | 18 | 43.9 | 11 | 26.8 |
| ስለ ርዕሱ ውስን እውቀት ያዘለ ጥቂት ፍሬ ነገር ብቻ ያለበት ወዘተ 16 — 20% | 20 | 48.8 | 4 | 9.8 | 12 | 29.3 | 24 | 58.5 |
| ስለ ርዕሱ ምንም እውቀት ያላዘለ በደንብ ያልተብራራ ወዘተ 1-15 % | 6 | 14.6 | - | - | 6 | 14.6 | 3 | 7.3 |
| አጠቃላይ | 41 | 100 | 41 | 100 | 41 | 100 | 41 | 100 |

በሰንጠረዥ 2 እንደሚታየው በይዘት ችግሮች ዙሪያ በመምህራን የተሰጡት ምጋቤ ምላሾች የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ድርሰት አጠቃላይ 41 ተማሪዎች የተፈተኑ ሲሆን በዚህ ውስጥ 20 ተማሪዎች 48.8 የሆነውን ከፍተኛ ቁጥር የያዘው ስለ ርዕሱወስን እውቀት ያዘለጥቂት ፍሬ ነገር ብቻ ያለበት ድርሰት የጻፉ ናቸው፡፡ የቀሩት በመቶኛ ስሌት 10

ተማሪዎች 24.4 6 ተማሪዎች 14.6 እና 5 ተማሪዎች 12.2 የሚሆኑት ምጋቤ ምላሾች እንደቅደም ተከተላቸው ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ ስለ ርዕሱ ያልተሟላ እውቀት ያዘለ እና ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ በሚለው ምላሽ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡

በጥብቅቡድኑቅድመ ድርሰት መፃፍ ፈተና አጠቃለይ 41 ሲሆኑ ከእዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ 18 ተማሪዎች 43.9 የሚለው ምጋቤ ምላሽ ነው፡፡ የተቀሩት በመቶኛ ስሌት 12 ተማሪዎች 29.3፣ 6 ተማሪዎች 14.6፣5 ተማሪዎች 12.2 የሚሆኑት ምጋቤ ምላሾች እነደ ቅደም ተከተላቸው ስለ ርዕስ ውስን እውቀት ያዘለ ፣ ስለ ርዕሱ ምንም እውቀት ያላዘለ እና ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ የሚል ምላሽ የተሰጠባቸው ድርሰት የጻፉ ተማሪዎች ናቸው፡፡

በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የቅድመ ድርሰት ማጻፍ ልዩነት በተመለከተ ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት የያዘ በሚለው ሁለቱም 12.2 ሲሆኑ በእዚህ ነጥብ ላይ ልዩነት የለም፡፡ ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት የያዘ በሚለው የሙከራ ቡድኑ 24.4 ሲሆን ጥብቅ ቡድኑ 43.9 ነው፡፡ በዚህኘው ነጥብ ያለው ልዩነት መኖሩን ያሳያል ፡፡ ስለ ርዕስ ውስን እውቀት ያዘለ በሚለው የሙከራ ቡድኑ 48.8 ሲሆን የጥብቅ ቡድኑ ደግሞ 29.3 ነው በዚህ መካከል ያለውን ልዩነት ያለ ሲሆን ስለ ርዕሰ ምንም እውቀት ያልያዘ በሚለው 14.6 የሙከራ ቡድን ሲሆን 14.6 ደግሞ የጥብቅ ቡድኑ ነው፡፡ በእዚህኛው ነጥብ መካከል የነጥብ ልዩነት አይታይበትም፡፡

በአጠቃላይ በይዘት ላይ ተመስርቶ የተሰጠው የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ስለ ርዕስ የተሟላ እውቀት የያዘ በሚለው ስለ ርዕሱ ምንም እውነት ያላዘለ በሚለው ነጥብ ዘሪያ ልዩነት አያሳይም የሙከራ ቡድኑና የጥብቅ ቡድኑ መካከል የነጠብ ልዩነትን የሚያሳየው ስለ ርዕስ መካከለኛ እውቀትና ስለ ርዕሱ ውስን እውቀት የያዘ በሚል ላይ እንደሆነ ነው፡፡

በድህረ ድርሰት መፃፍ ዙሪያ የሚታየው በይዘት ችግሮች ለሙከራ ቡድኑ መምህራን የሰጡት ምጋቤ ምላሾች ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ 27 ተማሪዎች 65.8 ሲሆን የቀሩት በመቶኛ ስሌት 10 ተማሪዎች 24.4 ና 4 ተማሪዎች 9.8 የሚሆኑት ምላሾች እንደቅደም ተከተላቸው ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ ሲሆን

ሌላው ስለ ርዕሱ ውስን እውቀት ያዘለ ነው፡፡ በእዚህ በድህረ ድርሰትመፃፍ ጊዜስለ ርዕሱ ምንም እውቀት ያላዘለ ድርሰት እንዳልተፃፉ ያሳያል፡፡

በድህረ ድርሰት መጻፍ በጥብቅ ቡድኑ መምህራን የሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ስለ ርዕሱ ውስን እውቀት የያዘ 24 ተማሪዎች 58.5 ሲሆን የቀሩት በመቶኛ ሲሰላ 11 ተማሪዎች 26.8፣3 ተማሪዎች 7.3 እና 3 ተማሪዎች 7.3 ናቸው እነዚህ እንደ ቅደም ተከተላቸው ሲገለፅ ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ፣ ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለና ስለርዕሱ ምንም እውቀት ያላዘለ የሚሉት ናቸው፡፡

በአጠቀላይ በድህረ ድርሰት መፃፍ ዙሪያ በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ ዙሪያ በይዘት ላይ ተመስርቶ የተሰጠው የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የሚያሳየውን ልዩነት ስለ ርዕሱ የተሟላ እውቀት ያዘለ በሚለው በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለው ልዩነት 58.5 የሙከራቡድኑ አብላጫ ነጥብን ያመለክታል፡፡ ስለ ርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ በሚለው ደግሞ የጥብቅ ቡድኑ አብላጫውን ያመላክታል፡፡ ስለ ርዕሱ ውስን እውቀት ያዘለ በሚለው ደግሞ የጥብቅ ቡድኑ መብለጡን ያሳያል ፡፡ በመጨረሻም ስለ ርዕሱ ምንም ነጥብ ሳይኖረው የጥብቅ ቡድኑ 7.3 ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በይዘት ዙሪያ በሙከራ ቡድንና በጥብቅ ቡድን በቅድመ ድርሰት መፃፍና በድህረ ድርሰት መፃፍ መካከል መምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት እና ባለመስጠት መካከልልዩነት መኖሩን ያሳያል ይህውም የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በቅድመ ድርሰት መፃፍ ዙሪያ ልዩነቱ አንፃራዊ ሲሆን በድህረ ድርሰት መፃፍ ላይ ሰፋ ያለ ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ላይ ይዘትን በተመለከተ መምህራን የሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የድርሰት መፃፉ ልምዳቸውን ያሻሽላል ለማለት ያስደፍራል፡፡

ሌላው የመፃፍ ችሎታና ለማዳበር በተማሪዎች የድርሰት መፃፍ ፈተና ላይ አደረጃጀትን በተከታታይ መመልከት እንደሚገባ ድርሳናት ይጠቁማሉ (Shih 1986)፡፡ ስለዚህ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ በአደረጃጀት ችግሮች ላይ የሚያተኩሩ ምጋቤ ምላሾች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ 2በአደረጃጀት ላይ ተመስርተው የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኛ ሲሰላ

| አደረጃጀትን የሚያመላክቱ የትኩረት ነጥቦች ከ20% | የሙከራ ቡድን | | | | የጥብቅ ቡድን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት ሀሣቦቹ በግልፅ የተቀመጠበት 20 -18% | 3 | 7.1 | 18 | 43.9 | 5 | 12.2 | 2 | 4.8 |
| በወጉ ያልተደራጀ ና እንደ ነገሩ የቀረቡበት ይህም ሆኖ ግን ዋናውን ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት 17-14% | 15 | 36.5 | 18 | 43.9 | 18 | 43.9 | 11 | 26.8 |
| ርቱዕነት የማይታይበት ሀሣቦች የተምታቱበት ወይም ያልተያያዙበት 13-10% | 19 | 46.3 | 5 | 12.2 | 18 | 43.9 | 23 | 56.1 |
| ምንም መልዕክት የማያስተላልፉ ምንም ዓይነት የሀሣብ አደረጃጀት የማይታይበት 9-7% | 4 | 9.7 | - | - | - | - | 5 | 12.2 |

ከለይ ካለው ሰንጠረዥ 3 እነደምንገነዘበው የአደረጃጀት ችግሮችን በተመለከተ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ድርሰት ፈተና የተሰጡ ምጋቤ ምላሾች አጠቃላይ 41.ሲሆኑ በመቶኛ ስሌት 19 ተማሪዎች 46.3 ያህሉ ርቱዕነት የማይታይበት ሀሣቦች የተምታቱበት ወይም

ያልተያያዘበት ስር የሚጠቀስ ሆኖ ከፍተኛውን ቁጥር ይዟል፡፡ ቀሪዎቹ በወጉ ያልተደራጀ እንደ ነገሩ የቀረበበት ይህም ሆኖ ግን ዋናው ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት፣ ምንም መልዕክት የማያስተላልፍ ምንም አይነት የሀሣብ አደረጃጀት የማይታይበትና ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት እንዲሁም ሀሣቦቹ በግልፅ የተቀመጡበት ደግሞ እንደ ተቀመጡበት ሁኔታ 15 ተማሪዎች 36.5፣ 4 ተማሪዎች 9.7 እና 3 ተማሪዎች 7.1 ከመቶ አግኝተዋል፡፡

በጥብቅ ቡድን የቅድመ ድርሰት መፃፍ ፈተና የተሰጡ በአደረጃጀት ዙሪያ የተሰጡ ውጤቶች አጠቃላይ 41.ሲሆኑ በመቶኛ ስሌት 18 ተማሪዎች 43.9 ያህሉ በውጉ ያልተደራጀና እንደ ነገሩ ያቀረቡበት ይህም ሆኖ ግን ዋናውን ሀሳብ ተላይቶ የሚታወቅበት እና እንደዚሁ ተመሳሳይ ነጥብ ያለው 18 ተማሪዎች 43.9 ያህሉ ርቱዕነት የሚታይበት ፣ ሀሳቦቹ የተምታታበት ወይም ያልተያያዙበትን ያመለክታል፡፡ በመቀጠልም 5 ተማሪዎች 12.2 ያህሉ ደግሞ ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት ሀሳቦቹ በግልፅ የተቀመጡበትን ያመላክታል፡፡

በአጠላይ በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል በቅድመ ድርሰት ፈተና አደረጃጀት የሚያመለክቱ የትኩረት ነጥቦች መካከል እኩል አለመሆኑን ያሳያል ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት ሀሳቦቹ በግልፅ የተቀመጡበት በሚለው ነጥብ ስር የጥብቅ ቡድኑ የሙከራ ቡድኑን ብልጫ አሳይቷል፡፡ በወጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረቡበት ይህም ሆኖ ግን ዋናውን ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት በሚለው የጥብቅ ቡድኑ የሙከራ ቡድኑን ብለጫ አሳይቷል፡፡ ርዕቱነት የማይታይበት ሀሳቦቹ የተምታቱበት ወይም ያልተያያዙበት በሚለው ደግሞ የሙከራ ቡድኑ የጥብቅ ቡድኑን ብልጫ ያሳያል፡፡ ሌላው ምንም መልዕክት የማይታላለፍበት ምንም አይነት የሀሣብ አደረጃጀት የማይታይበት በሚለው ነጥብ ስር የሙከራ ቡድኑ 9.7 ሲያስመዘግብ የጥብቅ ቡድኑ የለውም፡፡በአደረጃጀት ዙሪያ ሲታይ ከሙከራ ቡድኑ ይልቅ የጥብቅ ቡድኑ በቅድመ ድርሰት ፈተና ላይ ደህና ውጤት ያስመዘገበ ይመስላል፡፡

የሙከራ ቡድን ድህረ ድርሰት አደረጃጀትን የሚያመላክቱ የትኩረት ነጥቦችን በተመለከተ ከፍተኛውን ነጥብ ያስመዘገቡት ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት ሀሣቦቹ በግልፅ የተቀመጡበት በሚለው 43.9 እና በወጉያልተደራጀ እንደነገሩ የቀረቡበት ይህም ሆኖ ግን ዋናውን ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት 43.9 ሲሆን፣ በሁለቱ ላይ ተመሳሳይ ውጤት ሲሆን

በሶስተኛነት 12.2 ደግሞ ርዕቱነት የሚታይበት ሀሳቦች የተምታቱበት ያልተያያዘበት በሚለው ነው፡፡

ከዚህ እንደምንረዳው ከቅድመ ድርሰቱና ከድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ይህ ቡድንም የሙከራ ቡድኑ በመሆኑ በተከታታይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አግኝተው ድርሰት መፃፍን የተፈተኑ ቡድኖች ናቸው፡፡

የጥብቅ ቡድን ድህረድርሰት ፈተና አደረጃጀትን የሚያመላክቱ የትኩረት ነጥቦችን በተመለከተ ከፍተኛውን ነጥብ ያስመዘገቡት ርቱዕነት የማይታይበት፣ ሀሳቦች የተምታቱበት ወይም ያልተያያዙበት 23 ተማሪዎች 56.1 ሲሆን በውጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረቡበት ይህም ሆኖ ግን ዋናውን ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት የሚለው በሁለተኛ ደረጃ 11 ተማሪዎች 26.8 ሲሆን ምንም መልዕክት የማያስተላልፍ ምንም አይነት የሀሣብ አደረጃጀት የማይታይበት በሚለው 5 ተማሪዎች 12.2 በ3ኛ ደረጃ ነው፡፡ በመጨረሻም ርቱዕ የሆነ አገላለፅ የሚታይበት ሀሣቦች በግልጽ የተቀመጡበት ሲሆን ይህም 2 ተማሪዎች 4.8 መሆኑን ያሳያል ይህ በቅድመ ድርሰት መፃፍ ጋር ሲነፃፀር እያነሰ መምጣቱን ያሳያል ይህ ቡድን ምንም አይነት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሳይሰጣቸው የሚፅፉ ቡድኖች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አደረጃጀትና ችግሮች በሚያመላክቱ ነጥቦች ዙሪያ ያላቸው ትኩረት ተመጣጣኝ አለመሆኑ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን በሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ልምዳቸውን በማሻሻል ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ማለት ነው፡፡

ሌላው የተማሪዎች ድርሰት መጻፍ ችሎታ ለማዳበር በተማሪዎች የድርሰት መፃፍ ፈተና ላይ የቃላት ችግሮች በተከታታይ መመልከት እንደሚገባ በክለሳ ድርሰናት የጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የትኩረት አቅጣጫ በሚለው ስርKeh {1990} ይጠቁማሉ ፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ሰንጠረዥ በቃላት ችግሮች ላይ የሚያተኩሩ ምጋቤ ምላሾችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ሰንጨረዥ 3 ቃላትን በተመለከተ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመቶኛ ስሌት

| ቃላትን የሚያመላክቱ የትኩረት ነጥቦች 20% | የሙከራ ቡድን | | | | የጥብቅ ቡድን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | |
| | በቁጥር | በመቶ ኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| በሳል የሆነ የተዋጣለት የቃላት፡ የአባባሎች መረጣና አጠቃቀም የሚታይበት ወ.ዘተ. 20-18% | 2 | 4.9 | 13 | 31.7 | 2 | 4.9 | - | - |
| በበቂ ደረጃ የቀረበ አልፎ አልፎ የቃላት አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃላይ ስህተት ቢታይበትምምን ማለት እንደሆነ ሊገመት የሚችል 17-14 % | 16 | 39 | 21 | 51.2 | 22 | 53.6 | 12 | 29.3 |
| በውስን ደረጃ የቀረበ የቃላት የአባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት 13-10 % | 21 | 51.2 | 7 | 17 | 16 | 39 | 25 | 60.9 |
| የቃላት አባባሎች አጠቃቀም በጣም አነስተኛ የሆነ 9-7% | 2 | 4.9 | - | - | 1 | 2.4 | 4 | 9.7 |

በሰንጠረዥ 4 በግልፅ እንደሚያሳየው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ በተደጋጋሚ መሰጠቱ ለውጥ እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህውም ቃላትን የሚያመላክቱ ነጥቦች ስር የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ድርሰት ፈተና ላይ በሳል የሆነ የተዋጣለት የቃላት

የአባባሎች መረጣና አጠቃቀም ሚታይበት ወዘተ ከ20-18 ነጥብ የስመዘገቡ 2 ተማሪዎች 4.9 ሲሆን፤ ይህም በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ከፍተኛውን ቁጥር ያስመዘገቡ በውስን ደረጃ የቀረበ የቃላት/ አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት ድርሰት ፈተና 21 ተማሪዎች 51.2 ነው፡፡ በ2ኛ ደረጃ በበቂ ደረጃ የቀረበ አልፎ አልፎ የቃላት ቅርፅ መረጠና አጠቃቀም ስህተት ባይታይበትም ምን ማለት እንደሆነ ሊገመት የሚችል በሚለው 16 ተማሪዎች 39 ሲሆን በአራተኛነት የቃላት አባባሎች አጠቃቀም በጣም አነስተኛ  የሆነ የተጠቀሙት 2 ተማሪዎች 4.9 ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ቃላት የሚያመለክቱ ከ20% ያገኙት ከ13-10 ውስጥ ያሉት ላይ አብዛኛው ተማሪ እንዳለ ያሳያል፡፡

የጥብቅ ቡድን ቅድመ ድርሰት የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ውጤት በቃላት ስህተት ዙሪያ ከፍተኛውን ቁጥር የሚያሳየው በበቂ ደረጃ የቀረበ አልፎ አልፎ የቃላት አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ስህተት ቢታይበትም ምን ማለት እንዳሆነ ሊገመት የሚችል ማለትም ከጥሩ ደካማ 22 ተማሪዎች 53.6 ነው ፡፡ ቀሪዎች በውስን ደረጃ የቀረበ የቃላት አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት፣ በሳል የሆነ የተዋጣለት  የቃላት አባባሎች መረጣና አጠቃቀም የሚታይበት ወዘተ የቃላት አባባሎች አጠቃቀም በጣም አነስተኛ የሆነ እንደተቀመጠበት ሁኔታ 15 ተማሪዎች 39፣ 2 ተማሪዎች 4.9 እና 1 ተማሪ 2.4 በመቶኛ አግኝተዋል፡፡የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ድርሰት ፈተና እና የጥብቅ ቡድኑ የቅድመ የድርሰት ፈተና ሲነፃፀር አንጻራዊ የሆነ ልዩነት ያሳያል፡፡

የሙከራ ቡድን የድህረ ድርሰት መፃፍ ፈተና የቃላት አጠቃቀምን ችግር በተመለከተ አጠቃላይ የተሰጡ ምጋቤ ምላሾች 41 ሲሆኑ በመቶኛ ስሌት 21 ተማሪዎች 51.2 በበቂ ደረጃ የቀረበ አልፎ አልፎ የቃላት አባባሎች ቅርጽ መረጣና አጠቃቀም ስህተት ቢታይበትም ምን ማለት እንደሆነ ሊገመት የሚችል ውስጥ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ በሳል የሆነ የተዋጣለት የቃላት አባባሎች መረጣና አጠቃቀም የሚታይበት ወዘተ. በውስን ደረጃ የቀረበ የቃላት አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት ደግሞ እንደተቀመጡበት ሁኔታ 13 ተማሪዎች 31.7 እና 7 ተማሪዎች 17 በመቶ አግኝተዋል፡፡

በጥብቅ ቡድን ድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና ደግሞ አጠቃላይ 41 ሲሆን በመቶኛ ስሌት 25 ተማሪዎች60.9 ያህሉ በውስን ደረጃ የቀረበ የቃላት / አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋሚ ስህተት የሚታይበት ከፍተኛውን ቁጥር ይዟል፡፡ ቀሪዎቹ በበቂ ደረጃ የቀረቡ አልፎ አልፎ የቃላት አባባሎች ቅርፅ መረጣና አጠቃቀም ስህተት በይታይበትም ምን ማለት እንደሆነ ሊገመት የሚችል የቃላት አባባሎች አጠቃቀም በጣም አነስተኛ የሆነ ደግሞ እነደተቀመጡበት ሁኔታ 12 ተማሪዎች 29.3 4 ተማሪዎች 9.7 በመቶኛ አግኝተዋል በዚህ ቡድን ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘ አንድም ተማሪ አይገኝበትም

በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል በቅድመ ድርሰት መፃፍ አንፃራዊ ልዩነት ሲኖር በድህረ ድርሰት መፃፍ ጊዜ ግን ሰፊ ልዩነት ይታያል ይህውም ያመጣው የሙከራ ቡድኑ በተከታታይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በማግኘታቸው የተሻለ ውጤት እንዳመጡ መገመት ይቻላል፡፡

ሌላውተማሪዎችድርሰትየመፃፍችሎታንለማዳበርየመምህራንፅሁፋዊምጋቤ ምላሽውጤትበተመለከተበቋንቋአጠቃቀምመመልከትእንደሚገባክለሳ ድርሳናት (Shih 1986) ላይ ይጠቁማሉ፡፡ስለዚህየሚከተለውንሰንጠረዥበመመልከትየቋንቋ አጠቃቀምን ችግር የሚያመላክተው ሰንጠረዥ ይጠቁማል፡፡

**ሰንጠረዥ 4በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተመስርተው የተሰጡ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች በመቶኝ ሲሰላ**

| የቋንቋ አጠቃቀምን የሚያመለክቱ የትኩረት ነጥቦች 20% | የሙከራ ቡድን | | | | የጥብቅ ቡድን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| ረቀቅ ያለየቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታየቀረበበት ወዘተ 25-22% | 2 | 4.9 | 7 | 17 | 3 | 7.3 | - | - |
| የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራሆኖ መልዕክቱ ግን በደንብ የሚተላፍበት ወዘተ 21-19% | 8 | 19.5 | 21 | 51.2 | 8 | 19.5 | 10 | 24.3 |
| ረቀቅ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጐላ ችግር የሚታይበት ወዘተ 18-11% | 31 | 75.6 | 13 | 31.7 | 29 | 70.1 | 29 | 70.7 |
| በመሰረቱ የዐ.ነገር አመሰራረት በደንብ ያልተደራጀ ወዘተ 10-5% | - | - | - | - | - | - | 2 | 4.8 |

ከላይ ካለው ሰንጠረዥ እንደምንገነዘበው የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ ከ25% የሚገልፅ ነው፡፡ በሙከራ ቡድኑ የቅድመ ድርሰት ረቀቅ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጐላ ችግር የሚታይበት ወዘተ 31 ተማሪዎች 75.6 በመቶኛ ስሌት ከፍተኛውን የያዘ ሲሆን የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራ ሆኖ መልዕክቱ ግን በደንብ ሚተላለፍበት ወዘተ፣ ረቀቅ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታ የቀረበበት እንደ ቅደም ተከተሉ 8 ተማሪዎች 19.5 እና 2 ተማሪዎች 4.9 በመቶኛ አግኝተዋል፡፡

የጥብቅ ቡድን የቅድመ ድርሰት ውጤት በተመለከተ ረቀቅ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጐላ ችግር የሚታይበት 29 ተማሪዎች 70.7 ከፍተኛ ቁጥር የያዘ ሲሆን ሌሎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ተራ ሆኖ መልዕክቱ ግን በደንብ ሚተላለፍበት ወዘተ ረቀቅ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታ የቀረበበት ወዘተ በተቀመጡበት ሁኔታ 8 ተማሪዎች 19.5 እና 3 ተማሪዎች 7.3 ነው፡፡ ከዚህ እነደምንረዳው በሙከራ ቡድኑ እና በጥብቅ ቡድኑ የቅድመ ድርሰት መፃፍ መካከል የሰፋ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ይህም የሆነው በሁለቱም ውስጥ ምንም አይነት የተለያየ እገዛ ስለሌለ የውጤት መለያየት እንደማይኖር ያረጋግጥልናል፡፡

በመቀጠል በሙከራ ቡድን ድርሰት መፃፍ የቋንቋ አጠቃቀም በተመለከተ የተሰጡ ምጋቤ ምላሾች ውጤት የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራ ሆኖ መልዕክቱ በደንብ የሚተላለፍበት ወዘተ 21 ተማሪዎቸ 51.2 በመቶ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ ነው፡፡ ረቀቅ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታ የቀረበበት ወዘተ እንደቅደም ተከተላቸው 13 ተማሪዎች 31.7 እና 7 ተማሪዎች 17 በመቶ አግኝተዋል፡፡ የጥብቅ ቡድኑ የድህረ ድርሰት መፃፍ የቋንቋ አጠቃቀም በተመለከተ ረቀቅ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጐላ ችግር የሚታይበት ወዘተ 29 ተማሪዎች 70.7 ከፍተኛውን ነጥብ ሲይዙ የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራ ሆኖ መልዕክቱ ግን በደንብ የሚተላለፍበት ወዘተ ከመሰረቱ የዐ.ነገር አመሰራረት በደንብ ያልተደራጀ የሚለው እንደ ቅደም ተከተሉ 10 ተማሪዎች 24.3 እና2 ተማሪዎች 4.8 በመቶኛ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ በድህረ ድርሰት መፃፍ ዙሪያ ያለውን መረጃው የሚያሳየውልዩነት መኖሩን ሲሆን ልዩነቱም የሙከራ ቡድኑ በድርሰት አጻፃፋቸው ላይ ከቅድመ ድርሰቱ ጋር ሲነፃፀር መሻሻል መኖሩን ሲያሳይ በጥብቅ ቡድኑ ግን በቅድመ ድርሰትና በድህረ ድርሰት መካከል የመሻሻል ሁኔታን አያሳይም ይህ እነደሚገልጸው ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች ድርሰት ላይ እየሰጡ ድርሰት እንዲፅፉ ማድረግ ለተማሪዎች ድርሰት መፃፍ ችሎታ መዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ሲሆን ምንም አይነት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት ላይ አለመስጠት ግን የተማሪዎች ድርሰት አፃፃፍ ችሎታ እንደሚቀንስ ያሳያል፡፡በመጨረሻም በተማሪዎች ድርሰት ላይ መምህራን የሰጡትን ምጋቤ ምላሽ በቅርጽ ላይ የሚያሳዩትን ስህተቶች የሚያሳይ ሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 5በቅርጽ ችግሮች ላይ ተያይዘው የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ  የመቶኛ ሲሰላ

| በቅርጽ ላይ የሚያመለክቱ የትኩረት ነጥቦች በ5% | የሙከራ ቡድን | | | | የጥብቅ ቡድን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | | ቅድመ ድርሰት | | ድህረ ድርሰት | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት ከፍተኛ ነጥቦች 5% | - | - | 7 | -17 | - | - | - | - |
| አልፎ አልፎ የስርዓተ ነጥብና የሆኄያት ችግር የሚታይበት ወዘተ 4% | 2 | 4.9 | 22 | 53.6 | - | - | - | - |
| ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓት ነጥብ የሆኄያት አጣጣል ችግር የሚታይበት ወዘተ 3% | 13 | 31.7 | 10 | 24.4 | 7 | 17 | 11 | 26.8 |
| የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት የሌለው ስርዓት ነጥብ የሆኄያት አጣጣልና የአንቀፅ አከፋፈል ወዘተ ችግር ጉልቶ የሚታይበት 2% | 26 | 63.4 | 2 | 4.9 | 34 | 82.9 | 30 | 73.2 |

በሰንጠረዥ 6 እንደሚታየው በቅርጽ ችግሮች ዙሪያ የተሰጡ ምጋቤ ምላሾች የሙከራ ቡድን ቅድመ ድርሰት ፈተና የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት የሌለው ስርዓተ ነጥብ፣ የሆሂያት አጣጣልና የአንቀፅ አከፋፈል ወዘተ ችግር ጐልቶ የሚታይበት 26 ተማሪዎች 63.4 በመቶ ከፍተኛውን ነጥብ የያዘ ነው፡፡ የቀሩት በመቶኛ ስሌት 13 ተማሪዎች 31.7፣ 2 ተማሪዎች 4.9 የሆኑት እንደ ቅደም ተከተላቸው ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓትነጥብ የሆሂያት

አጣጣል ችግር የሚታይበት እና አልፎ አልፎ የስርዓተነጥብ የሆሄያት ችግር የሚታይበት ወዘተ መሆኑን ያሳያል፡፡

የጥብቅ ቡድን ቅድመ ድርሰት ፈተና ደግሞ 34 ተማሪዎች 82.9 በመቶ የሚሆነው የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት የሌለው ስርዓተ ነጥብ፣ የሆሄያት አጣጣልና የአንቀጽ አከፋፈል ወዘተ ችግር ጉልቶ የሚታይበት ከፍተኛውን ቁትር ይዟል፡፡ ሌላው 7 ተማሪዎች 17 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓተ ነጥብ፤የሆሄያት አጣጣል ችግር የሚታይበት ነው፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት የሚቻለው በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ የጉላ ልዩነት እንደሚያሳይ ነው፡፡

የሙከራ ቡድኑ የድህረ ድርሰት መፃፍ ፈተና ውጤት 22 ተማሪዎች 53.6 አልፎ አልፎ የስርዓተ ነጥብና የሆሄያት ችግር የሚታይበት በከፍተኛውን ቁጥር የዟል፡፡ ሌላው 10 ተማሪዎች 24.4 እና 2 ተማሪዎች 4.9 እንደ አቀማመጣቸው ቅደም ተከተል ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓተ ነጥብና የሆሄያት አጣጣል ችግር የሚታይበት፣የቅርጽ አጠቃቀም ብቃቱ ከፍተኛ የሆነ እና የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት የሌለው ስርዓተ ነጥብ የሆሄያት አጣጣልና የቅርጽ አከፋፈል ወዘተ ችግር ጉልቶ የሚታይበት ነው፡፡

የጥብቅ ቡድን የድህረ ድርሰት ፈተና ውጤት ደግሞ 30 ተማሪዎች 73.2 በመቶ የሚሆነው ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው የቅርጽ አጠቃቀም ብቃት የሌለው ስርዓተ ነጥብ የሆሄያት አጣጣል የአንቀጽ አከፋፈል ወዘተ ችግር ጉልቶ የሚታይበት ነው፡፡11 ተማሪዎች 26.8 በመቶ የሚሆነው ተደጋጋሚ የሆነ የስርዓተ ነጥብ አጣጣል ችግር የሚታይበት ወዘተ መሆኑን ይገልፃል፡፡

**ሰንጠረዥ6 አጠቃላይ የሙከራ ቡድንና የጥብቅ ቡድን አማካይ ውጤት**

| | | | ድርሰትን ለማረም የሚያስችል የትኩረት ነጥቦች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተጠኝ ቡድን | የተማሪ ብዛት | የፈተና ጊዜ | ይዘት 30% | አደረጃጀት 20% | ቃላት 20% | የቋንቋ አጠቃቀም25% | ቅርጽ 5% | ድምር 100% |
| የሙከራ ቡድን | 41 | ቅድመ ድርሰት | 19.7 | 14 | 14.1 | 17.7 | 2.5 | 68 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድህረ ድርሰት | 25 | 16.8 | 16.6 | 19.3 | 3.9 | 81.7 |
| የጥብቅ ቡድን | 41 | ቅድመ ድርሰት | 20.5 | 14.6 | 14.3 | 18.3 | 2.3 | 70.2 |
| | | ድህረ ድርሰት | 19.3 | 13.78 | 13.5 | 17.27 | 2.5 | 67 |

ከሰንጠረዡ የምንረዳው የሙከራ ቡድኑ ከቅድመ ድርሰት ፈተና አማካይ ውጤቱ 68 ሲሆን የድህረ ድርሰት ፈተናው አማካይ ውጤት 81.7 መሆኑን ያሳያል፡፡በተጨማሪ የጥብቅ ቡድኑ ቅድመ ድርሰት አማካይ ውጤት 70.2 ሲሆን ድህረ ድርሰት 66.4 መሆኑን ይገልጻል፡፡መምህራን በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው ካረሙት ውስጥ ከሁለቱም ቡድኖች መሻሻል ያሳየው በቅርጽ አጠቃቀማቸው ላይ ነው፡፡ይህም በክለሳ ድርሳናት 2.1.4.1 ስር እንደ Fathman and Whalley (1990} ገለጻ አንዳንድ መምህራን ለስርአተ ነጥብ፣ለፊደል አጣጣል፣ለሰዋሰው አገላለጽና ለመሳሰሉት ትኩረት ሲሰጡት አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተመለየ ሁኔታ ለይዘት፣አደረጃጀት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡በተጨማሪ የቋንቋ መምህራንምጋቤ ምላሻቸው ከይዘት ይልቅ በቅርጽላይ ትኩረት ማድረጉ ለመጻፍ ኪሂል የተሸለና ትክክለኛ አካሄድ እንደሆነም kek 1990Cohen and Cavalcant 1990 Zamel 1985 ይገልጻሉ፡፡

የሚቀጥሉት ሰንጠረዦች በሙከራ ቡድንና በጥብቅ ቡድን መካከል ያለ በመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠትና ባለመስጠት መካከል የለውን የውጤት ልዩነት በቲ-ቴስት ተገልጿል፡፡

ሰንጠረዥ7 የቅድመ ድርሰት ፈተና የመምህራን ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽበ"Independ%ent Sample t-test for control and experimental group"

| ተጠኝ ቡድን | የተማሪ ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ ልይይት | የቲቴስት ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የተዛምዶ ልኬት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 41 | 68.2463 | 6.48071 | -2.200 | -1.551 | 80 | 0.125 |
| የጥብቅ ቡድን | 41 | 70.4463 | 6.36039 | | | | |

በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ በቅድመ ድርሰት ፈተና ጊዜ በተማሪዎች ውጤት መካከል በእስታስቲክየፒ ዋጋ 0.125ከቲ-ቴስት ዋጋ (ከ0.05) በመብለጡ በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ምንም አይነት ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡

ሰንጠረዥ 8 የድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በ"Independendent Sample T-test for control and experimental group"

| ተጠኝ ቡድኖች | የተማሪዎች ቁጥር | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ ልይይት | የቲ-ዋጋ ቲ-ቴስት | የነጻነት ደረጃ | የተዛምዶ ልኪት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | 41 | 81.8488 | 6.41697 | 14.68537 | 8.808 | 80 | 0.000 |
| የጥብቅ ቡድን | 41 | 67.1634 | 8.53272 | | | | |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና በሙከራ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለው የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ የፒ ዋጋ 0.000 ሆኖ ከ0.05 ስለሚያንስ ልዩነት መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ይህም የሚያመላክተው የሙከራ ቡድኑ

በመምህራን ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ምክንያት ከላይ በተመዘገበው የቅድመ ድርሰት መጻፍ ፈተና ውጤት የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ማሻሻሉንና አለማሻሻሉን ለማረጋገጥ በRepeated Measures የስታስቲክስ ስሌት ለማየት ተሞክሯል

**ሰንጠረዥ9 በጥብቅ ቡድንና በሙከራ ቡድን መካከል ያለ የድርሰት መጻፍ ፈተና ውጤት ልዩነት በ"Repeated Measues sampl T-test"**

| ተጠኝ ቡድኖች | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ ልይይት | ቲ-ቴስት | የነጻነት ደረጃ | የተዛምዶ ልኬት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የጥብቅቡድን ቅድመ ድርሰት ፈተና | 70.4463 | 6.36039 | 3.28293 | 2.072 | 40 | 0.51 |
| የጥብቅ ቡድን ድህረ ድርሰት ፈተና | 67.1634 | 8.53272 | | | | |
| የሙከራቡድንቅድመ ድርሰት ፈተና | 68.2463 | 6.48071 | -13.604 | -10.615 | 40 | 0.000 |
| የሙከራቡድን ድህረ ድርሰት ፈተና | 81.8488 | 6.41697 | | | | |

ከሰንጠረዡ የምንረዳው በጥብቅ ቡድኑናበሙከራ ቡድኑ መካከል ያለውን የድርሰት መጻፍ ፈተና ውጤት የሚያሳይ ሲሆን ውጤቱም የጥብቅ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ፈተና የፒ ዋጋ 0.51 ከ0.05 በላይ ስለሆነ ልዩነት እንደሌለ ያመለክታል፡፡

በሙከራ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ድርሰት መጻፍ ፈተና ውጤት መካከል አማካይ ልይይት -13.604ሲሆን የተ-ቴስት ዋጋ ደግሞ-10.615 ነው፡፡የፒ ዋጋ 0.00 ሆኖ ከ0.05 በታች በመሆኑ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል፡፡ከመረጃው ስናይ የመምህራን ጽሑፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን የድርሰት መጻፍ ችሎታ እንደሚያዳብር ይገልጻል፡፡

### 4.1.2 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ትንተና

ለዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ካገለገሉት መካከል የጽሁፍ መጠይቅ አንዱ ነው፡፡ አላማውም ተማሪዎች ለሚፅፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያለውን አስተዋፅኦ ለመፈተሽ የሚያገለግል መረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ ለመረጃው አተናተን አመቺነት እንዲኖረው የጽሁፍ መጠይቅ በአይነታቸው ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 11የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ትንተና በመቶኛ ሲሰላ**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የተሰጡ አማራጭ መልሶች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በጭራሽ አልስማማም | | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | ድምር |
| 1 | ለፃፍኳቸውፅሁፎች መምህሬ የሚሰጡኝ ምጋቤ ምላሾች ስሜትን የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡ | 35 | 42.6 | 6 | 7.3 | 26 | 31.7 | 15 | 18.2 | 82 |
| 2 | ለምፅፈው ጽሁፍ የሚሰጡኝን ምጋቤ ምላሽ በቀላሉ ተረድቼ አስተካክላለሁ | 41 | 50 | 23 | 28 | 13 | 15.8 | 5 | 6.1 | 82 |
| 3 | የምፅፋቸው ፅሁፎች ሳልረሳቸው ታርመው ይመለሱልኛል | 63 | 76.8 | 13 | 15.8 | 3 | 3.6 | 3 | 3.6 | 82 |
| 4 | በምፅፈው ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩብኝን ስህተቶች ምጋቤ ምላሽ ስለሚሰጡኝ መምህሬን አመሰግናቸዋለሁ | 43 | 52.4 | 11 | 13.4 | 25 | 30.4 | 3 | 3.6 | 82 |
| 5 | መምህሬ የወሰዱትን ፅሁፍ አርመው ሳይመልሱልንና ስህተቴን ሳልረዳ ሌላ እንድፅፍ አያዙኝም | 43 | 52.4 | 28 | 34.1 | 4 | 4.8 | 7 | 8.5 | 82 |
| 6 | መምህሬ ልረዳቸው የምችለውን መልክቶች በመጠቀም ምጋቤ ምላሽ ይሰጡኛል | 37 | 45.1 | 4 | 4.8 | 32 | 39 | 9 | 10.9 | 82 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬን የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ በምፅፈው ድርሰት የሀሣብ ፍስትና አደረጃጀት ዙሪያ ትኩረት ያደርጉልኛል፡፡ | 35 | 42.6 | 7 | 8.5 | 37 | 45 | 4 | 4.8 | 82 |
| 8 | ለምፅፋቸው ፅሁፎች የመምህሬን ምጋቤ ምላሽ እመለከታለሁ | 44 | 53.6 | 26 | 31.7 | 6 | 7.3 | 6 | 7.3 | 82 |
| 9 | መምህሬ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በምፅፈው | 40 | 48.7 | 1 | 1.2 | 35 | 42.6 | 6 | 7.3 | 82 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድርሰት ይዘትና ቅርፅ ነክ ላይ ትኩረት ያደረጉልኛል | | | | | | | | | |
| 10 | የመምህራን ምጋቤ ምላሽ የቋንቋ አጠቃቀምና ስርዓተ ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ | 25 | 30.4 | 16 | 19.5 | 26 | 31.7 | 15 | 18.2 | 82 |
| 11 | መምህሬ የሚያደርጉልኝ ድጋፍ ለምፅፈው ድርሰት በእጅጉ ጠቅሞኛል | 29 | 35 | 12 | 14.6 | 35 | 42.6 | 6 | 7.3 | 82 |
| 12 | መምህሬ የሚሰጡኝ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች አወንታዊ ገፅታዎች አሏቸው፡፡ | 25 | 30.4 | 16 | 19.5 | 35 | 42.6 | 6 | 7.3 | 82 |

ሰንጠረዠ 10 በግልፅ እነደሚያሳየው ተማሪዎች ለሚፅፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመፃፍ ችሎታቸውን በማደበር በኩል ያለውን አስተዋፅኦ ያሳያል እንዲሁም ከመጠይቅ ነጥቦች ተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 12 በአቀማመጣቸው ቅደም ተከተል መሰረት በጣም እስማማለሁ ያሉት ለ1ኛው ለጻፍኳቸው ጽሁፎች መምህሬ የሚሰጡኝ ምጋቤ ምላሾች ስሜትን የሚቀሰቅሱ ናቸው35 ተማሪዎች42.6፣ እስማማለሁ ያሉ 6 ተማሪዎች7.3 አልስማማም ያሉ 26 ተማሪዎች 31.7 መቶኛ በጭራሽ አልስማማም ያሉ ደግሞ 15 ተማሪዎች 18.2መሆኑን ያመላክታል፡፡

2ኛ ለምጽፈው ጽሁፍ የሚሰጡንን ምጋቤ ምላሽ በቀላሉ ተረድቼ አስተካክላለሁ በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት 41 ተማሪዎች50 በርካታ ተማሪዎች ሲሆኑ በመቀጠል እስማማለሁ ያሉት 23 ተማሪዎች 28 መቶኛአልስማማም13 ተማሪ 15.8 እና በጭራሽ አልስማማም 5 ተማሪዎች 6.1 በመቶኛ ናቸው፡፡ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች መምህራን የሚሰጧቸውን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ተረድተው ጽሁፋቸውን እንደሚያስተካክሉ ያሳያል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3 የምጽፋቸው ጽሁፎች ሳልረሳቸው ታርመው ይመለሱልኛል ለሚለው በጣም እስማማለው ያሉት ተማሪዎች 63 ተማሪዎች 76.8 በመቶ ከፍተኛውን ቁጥር የሚወክሉ ሲሆኑ እስማማለሁ ያሉት 13 ተማሪዎች 15.8 ናቸው ፡፡እንዲሁም አልስማማም ያሉት 13 ተማሪዎች 15.8ያህሉ ሲሆኑ በጭራሽ አልስማማም ያሉት ደግሞ 14 ተማሪዎች 16.7 ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፈተና ወረቀት ፈጥነው መመለሳቸውንና ይህም ተማሪዎች ለሰሩት ስህተት ወዲያውኑ ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ይገልጻል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4 በምጽፈው ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩብኝን ስህተቶች ምጋቤ ምላሽ ስለሚሰጡኝ መምህሬን አመሰግናቸዋለሁ በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት 43 ተማሪዎች 52.4 ሲሆኑ እስማማለሁ ያሉት ደግሞ 11 ተማሪዎች 13.4 ናቸው፡፡እንዲሁም አልስማማም ያሉት25 ተማሪዎች 30.4 ሲሆኑ በጭራሽ አልስማማም ያሉት ደግሞ 3 ተማሪዎች 3.6 ናቸው፡፡ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ስህተታቸው ሲገለጽላቸው ለማረምና ለማስተካከል እንዲሁም ለመለወጥ ዝግጁ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5 መምህሬ የወሰዱትን ጽሁፍ አርመው ሳይመልሱልንና ስህተቴን ሳልረዳ ሌላ እንድጽፍ አያዙኝም በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት 43 ተማሪዎች 52.4 ሲሆኑ እስማማለሁ ያሉት ደግሞ 28 ተማሪዎች 34.1 እንዲሁም አልስማማም ያሉት 4 ተማሪዎች 4.8 እና በጭራሽአልስማማም ያሉት7 ተማሪዎች 8.5 ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት በጣም እስማማለህ ያሉት በመሆናቸው ተማሪዎች ስህተታቸውን የሚያውቁት ከመምህራን ምጋቤ ምላሽ በመሆኑ የመምህራንን ከፍተኛ ተሳትፎ ለተማሬዎች የጽሁፍ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጥኦ እንዳለው ያሳያል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6 መምህሬ ልረዳቸው የምችለውንምልክቶች በመጠቀም ምጋቤ ምላሽ ይሰጡኛል በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት31 ተማሪዎች 45.1፤እስማማለሁ 4 ተማሪዎች4.8፤አልስማማም32 ተማሪዎች 40.2 እና በጭራሽ አልስማማም ያሉ ደግሞ 9 ተማሪዎች 10.9 ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ በምጽፈው ድርሰት የሀሳብ ፍሰትና አደረጃጀት ዙሪያ ትኩረት ያደርጉልኛል በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ 35 ተማሪዎች 42.6፤እስማማለሁ 6 ተማሪዎች 7.3፤አልስማማም38 ተማሪዎች 46.3እና በጭራሽ አልስማማም4 ተማሪዎች 4.8 ሲሆን በርካታው ተማሪ በጣም እስማማለሁ በሚለው ሀሳብ ውስጥ ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8 ለምጽፋቸው ጽሁፎች የመምህሬን ምጋቤ ምላሽ እመለከታለሁ ለሚለው ሃሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት 44 ተማሪዎች 53.6 ፤እስማማለሁ ያለ26 ተማሪዎች 31.7 ፤ አልስማማም ያሉ 6 ተማሪዎች 7.3 ሲሆኑ በጭራሽ አልስማማም ያሉ ደግሞ 6 ተማሪዎች 7.3 ናቸው፡፡ይህ የሚያመለክተው ተማሪዎች ስለትክክለኛነታቸው ከመምህር ምላሽ እንደሚጠብቁ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9 መምህሬ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ በምጽፌው ድርሰት ይዘትና ቅርጽ ነክ ላይ ትኩረት ያደርጉልኛል በሚለው ሃሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉ40 ተማሪዎች 48.7፤እስማማለሁ 1 ተማሪ1.2፤ አልስማማም 35 ተማሪዎች 42.6 እና በጭራሽአልስማማም ያሉትደግሞ 6 ተማሪዎች7.3 ናቸው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 10 የመምህሬ ምጋቤ ምላሽ ቋንቋ አጠቃቀምና ስርአተ ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ በሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ 25 ተማሪዎች30.4፤እስማማለሁ16 ተማሪዎች 19.5 ፤አልስማማም26 ተማሪዎች 31.7 እና በጭራሽ አልስማማም ያሉት ደግሞ 15ተማሪዎች 18.2 ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 11 መምህሬ የሚያደረጉልኝ ድጋፍ ለምጽፌው ድርሰት በእጅጉ ጠቅሞኛል በሚለው ሀሳብ ላይ በጣም እስማማለሁ ያሉ 29 ተማሪዎች 35 እስማማለሁ ያሉ 12 ተማሪዎች 14.6፤አልስማማም35 ተማሪዎች 42.6 እና በጭራሽ አልስማማም 6 ተማሪዎች 7.3 የሀሉ ናቸው፡፡

ተራ ቁጥር 12 መምህሬ የሚሰጡኝ ጽሁፋዊ ምጋቤምላሾች አወንታዊገጽታዎች አሏቸው ለሚለው ሀሳብ በጣም እስማማለሁ ያሉት 25 ተማሪዎች 57.3፤እስማማለሁ ያሉ 16 ተማሪዎች 19.3፤አልስማማም1ተማሪ1.2 እና በጭራሽ አልስማማም ያሉ ደግሞ1ተማሪ1.2ናቸው፡፡

በተጨማሪ ለተማሪዎች ከተሰጣቸው ክፍት ጥያቄዎች1ኛው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች ትኩረት ምን ላይ ነው? ችሎታን ለማዳበር የሚረዳው ምጋቤ ምላሽ የትኛው ነው? ተብሎ ለቀረበላቸው ክፍት የፅሁፍ መጠይቅ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሾች መምህሬ የሚሰጡኝ ምጋቤ ምላሽ ይዘት፣ ቅርፅ እንዲሁም ስርዓተ ነጥብና አደረጃጀት ላይ እንደሚያተኩሩ ገልፀዋል፡፡ ችሎታን ለማዳበር የሚረዳው ምጋቤ ምላሽም ሁሉም ምጋቤ ምላሾች ስህተትን የሚጠቁሙ በመሆናቸው ችሎታን ያዳብሩልኛል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡

2ኛው ጥያቄ የአማርኛ መምህራን በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉን በሚለው ጥያቄ ላይ መልሳቸው አዎ የሚል ነው፡፤ በተራ ቁጥር 3 ላይ ስለ አማርኛ መምህራችሁ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ ተጨማሪ አስተያየት ካላችሁ ለሚለው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሰጡት አስተያየት የመምህራን ምጋቤ ምላሽ የቋንቋ

አጠቃቀም ችሎታችንንያዳብርልናል፡፡ስህተታችንን አይተን እንድናስተካክል ማድረጋቸው ጥሩ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ሀሳቦች ከክለሳ ድርሳናት ላይ ገምጋሚ ፣ አጠናካሪና አስተካካይምጋቤ ምላሽ የተጠቀሱ ሲሆኑ የጽሁፍ መጠይቁም እነዚህን ያካተተ ነው በመሆኑም አብዛኛው 38 ተማሪዎች 46.3 በጣም እስማማለሁ፣ 14 ተማሪዎች 0.17 እስማማለሁ፣ 23 ተማሪዎች28 በመቶ አልስማማምና 7 ተማሪዎች 0.08 በመቶ በጭራሽ አልስማማም የሚል ውጤት ትንተናው ያሳያል፡፡ከዚህ የምንረዳው የጽሁፍ መጠይቁ የቀረበው ለሁለቱም ተጠኝ ቡድኖች ስለሆነ በጥናቱ ዙሪያ ያሉትን ጥያቄዎች በልምምዳቸው ወቅት የተከናወነውን የሚያንጸባርቅ በመሆኑ የትንተናው ውጤትም አንጻራዊ ነው፡፡

## 4.1.3የቃለ መጠይቅ ትንተና

ሌላኛው ለዚህ ጥናት ትንተና መረጃ መሰብሰቢያ ሆነው ካገለገሉት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ አብይ አላማው ተማሪዎች ለሚፅፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመፃፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው፡፤ የሚል ሲሆን ጥያቄዎቹ የተዘጋጁት የጥናቱን አላማ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች እንደ ፅሁፍ መጠይቅ ሁሉ በአጥኝዋ ተዘጋጅቶ በአማካሪ ከተገመገመው በኋላ አስፈላጊውን ማሻሻያ ተደርጐባቸው ቀርበዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 12የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

| የትምህርት ቤት ስም | የመምህራን ብዛት | | | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | የመጀመሪያ ድግሪ |
| ወገሬ | 1 | 3 | 4 | 4 |
| ጦል | 1 | 1 | 2 | 2 |
| ድምር | 2 | 4 | 6 | 6 |

**ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና የሰጡት ምላሽ**

በጥያቄ አንድ ላይ ተማሪዎች በሚፅፉት ድርሰት መምህራን የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አላማ ምንድነው ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራኖች የሰጡት ምላሽ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች የምንሰጥበት አላማ የሚፅፉት ፅሁፉ የሀሣብ ቅደም ተከተል እንዲኖረው በፅሁፍ ወቅት እየፈጠሯቸው ያለውን ወይም መጻፍ የፈለጉትን በተገቢው መንገድ እንዲፅፉ ማስቻል እንደሆነ ገልፀዋል ( Block and Man 1995) የፅህፈት ኪሂል መደበር ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም ጥሩ የማስብ ብልሀትን ማረጋገጥና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል፡፡ ከሚለው ምሁራን ሀሣብ ጋር የሚመሳሰል ሲሆንምጋቤ ምላሻቸውን አይተው ማስተካከል መቻላቸው ፅሁፋቸውንም ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

ተማሪዎች በሚፅፏቸው ድርሰቶች ላይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መቼና እንዴት ይሰጣሉ ለሚለው ጥያቄ መምህር1 ድርሰት እንዴት እደሚጻፍ ቀድሜ አስተምራለሁ ከፃፉ በኋላም ስህተቶችን በማሳየት እንዲያሻሽሉ አደርጋለሁ መምህር 6 ደግሞ በማስተማር ጊዜ ተማሪዎች ፅፈው በሚያመጡት ፅሁፍ ላይ ነው ሲሉ የቀሩት መምህራን ድርሰቱን ፅፈው ካበቁ በኋላ በሚል ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

መምህራን የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾችና የተማሪዎች ፍላጐት አለመጣጣም በሚለው ርዕስ ስር መጀመሪያ ቋንቋ የፅህፈት ትምህርት ጥናት ቅኝት እንደተከተለው መምህራን ምጋቤ ምላሽ መስጠት የሚወዱት በጽሁፍ ሂደት እንደሆነ ተማሪዎች ደግሞ ፅሁፍ ካበቃ በኋላ ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፡፡ ከሚለው ጥናት ጋር ይህ ምላሽ የተማሪዎችን ፍላጐት በሚያሟላ መልኩ የሚሰሩ መሆኑንም ይገልፃል፡፡

ሶስተኛውን ጥያቄ በተማሪዎች ድርሰቶች ላይ የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች ትኩረት ምን ላይ ነው? መምህር 4 እና 6 ትኩረት የማደረገው ተማሪዎች በፈፅሙት ስህተት ላይ ነው፡፡ ብለዋል መምህር 5 ደግሞ በርዕስ መረጣው ጀምሬ የሀሳብ ሰንሰለታዊ ሂደቱን ትኩረት አደርጋለሁ ሲሉ ሌሎቹ፣ 1፣2፣3 ደግሞ ትኩረት የማደረገው አደረጃጀቱ፣ ይዘቱ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የእንቀፅ አመሰራረት፣ ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን፣ ቋንቋ አጠቃቀሙንና የስርዓተ ነጥቦች ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ገልፀወዋል፡፡ የፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አላማና ትኩረት በሚለው ስር በምጋቤ ምላሾች አሰጣጥ መስክ የተካሄዱ ጥናቶች ( Hedge 1988 Cohen a and Cavalcanti 1990 ዚቫ 1984፣Zamel 1985)

እንደሚጠቁሙት በምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ትኩረቶች ላይ ምሁራን እነደሚለያዩ ገልፀው የመምህራን ትኩረት በሁሉም ፅሁፎች ላይ እኩል አለመሆኑም ገልፀውታል፡፡

ጥያቄ 4 ከሚሰጡት ምጋቤ ምላሾች መካከል ለተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ይበልጥ የሚረዳው የትኛው ነው? ለሚለው ጥያቄ መምህራን 1፤2፤3፤6 ሁሉም አይነት ምጋቤ ምላሾች ለተማሪ ስህተት ማስተካከያ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ሲሉ መምህር 4 ደግሞ ይዘትና ቅርፅ ላይ ትኩረት በማድረግ የተማሪዎችን መፃፍ ችሎታ ለማዳበር እንደሚረዳ ይገልፃሉ፡፡ መምህር 5 ደግሞ ርዕስ መረጣው ከርዕሱ ጋር ያለው ተዛማጅነት አደረጃጀቱ ና ይዘቱ የቃላት አጠቃቀሙና ስርዓተ ነጥቦች ላይ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይበልጥእንደሚረዳ ገልፀዋል፡፡ ክለሳ ድርሳኑ ላይ ፍሪድማን (1978) በበኩሉ መምህራ ከቅርጽ ስህተቶች ይልቅ ለይዘትና ለአደረጃጀት ትኩረት መስጠታቸውን ሲጠቁሙ ቴይለር(1982) ሁሉም ተመራማሪዎች ለቅርፅና ለይዘት ትኩረት ስለመስጠት መስማማታቸውን ጠቁማል፡፤ ስለዚህ ይህም መረጃ የሚያመለክተው መምህራኖች በቅርፅና በይዘት ያተኩሩ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5 የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት መፃፍ ችሎታ ላይ አወንታዊ ገፅታ አለው ለሚለው ሁሉም መምህራን አዎ! የሚል ምላሽ ሰጥተዋል በተጨማሪ በክለሳ ድርሳኑ ላይ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች ስር እንደምሁራን ገለፃ ተማሪዎችን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲፅፉ ማድረግና ተገቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት የመፃፍ ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡ ከሚለው ሀሳብ ጋር የተያያዘ ምላሽ በመሆኑ በግልጽ አብራርተዋ፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6 በርዕስ ትኩረት ጽሁዳዊ ምጋቤ ምላሽ መሰጠት በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ አለው? በሚለው ጥያቄ መምህር 2 ተጽእኖ አይኖረውም እኔ በምሰጣቸው ፅኁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ላይ ስህተታቸውን በደንብ አትኩረው ካዩ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ስለሚኖረው ለጽሁፋቸው መሻሻል አስተዋጽኦ አለው፡፡ ምክንያቱም ተማሪወች የሚፈጽሙትን ስህተት በማየት ጽሁፋቸውን አስተካክለው እንዲጽፉ ስለሚረዳቸው ነው፡፡ መምህር 4 ተፅእኖ የለውም ስህተታቸውን በትኩረት እንዲያዩት ይረዳቸዋል፡፡ መምህር 5 ተጽእኖ የለውም ምጋቤ ምላሽ በምፅፍበት ጊዜ የተማሪዎችን ስሜት በማነሳሳት ንቁ ምላሽ እንዲሰጡኝ የደርጋል በዚሁ ተመሳሳይ መምህር 1፤3 ና 6 ተጽዕኖ የለውም ምክንያቱም ተማሪዎች ስህተታቸውን አውቀው

ያስተካክሉበታል፣ ትክክለኛውን የጽሁፍ ቅርጽና መደበኛ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓት ነጥብ ተጠቅመው እንዲፅፉ ይረዳቸዋል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡ ከክለሳ ድርሳናት ላይ አወንታዊና አሉታዊ ባህሪያቶች ውስጥ በ (Gipps et at 2004,58) ገለፃ ለተማሪው የሚቀርበው ምጋቤ ምላሽ ውጤታማ እንዲሆን የተማሪውን መፃፍ ክሂል ለማሻሻል እንዲረዳና ተስፋ አስቆራጭ እንዳይሆን መምህራን የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ አዎንታዊ መሆን ይኖርበታል የሚል ሲሆን ይህም ምጋቤ ምላሾች በተማሪዎች ድርሰት መፃፍ ችሎታ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ማሳየቱን ገልጿል፡፡ አሉታዊ ባህሪያቶች ደግሞ የምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት መፃፍ ችሎታ ላይ መጥፎ ተጽዕኖን የሚያሳይ ናቸው፡፡ ይህውም በክለሳ ድርሳናት ላይ አሉታዊ ባህሪያት ስር አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ ተማሪውን የፅሁፍ ስራ ትክክል አለመሆኑን በሚጠቁም መልኩ ቀለል ባለ ሁኔታ መገለፅ አለበት ያለበለዚያ ተማሪዎች ለፃፉት ነገር የሚሰጣቸውን አሉታዊ ምጋቤ ምላሾች ትችታዊ አድርገው ስለሚቆጥሩት ምን እንደሚሉ በወጉ ስለማያነቡት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡ በዚህም ጥናት ውስጥ መምህራን ከሰጡን ምለሽ ሲታይ ህንን አሉታዊና አዎንታዊ  ባህሪያትን ተረድተው በተማሪዎች የድርሰት ፅሁፍ ላይ ፅኁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የሰጡ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ጥያቄ 7 ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ከሚፈፅሙት የስህተት አይነት እርስዎ ትኩረት ሰጥተው የሚያርሙት የትኛውን ስህተት አይነት ነው? ለሚለው  ቃለ መጠይቅ መምህር 1 የሚፈፅሙት ስህተት ከበዛ የቃላት አጠቃቀሙንና የሀሳብ ፍሰቱን ቅደም ተከተል ላይ አትኩራለሁ መምህር 2 ዐ.ነገር አመስራረት  ይዘት ቅርጽና ስርዓተ ነጥብ ላይ አተኩራለሁ መምህር 3፣4፣6 ሁሉንም የፈፀሙትን ስህተት  እጠቀማለሁ መምህር 5 መጀመሪያ ትኩረት የምሰጠው ይዘት ላይ ሆኖ ሌሎችንም አያለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡  መምህራኖች ትኩረት ሰጥተው ያረሙት የስህተት አይነት ስህተቶቹ ከበዙ የቃላት አጠቃቀም፡፡ የሀሳብ ቅደም ተከተልን አርማለሁ ብለዋል፡፡ ይህም የታዩ ስህተቶችን በሙሉ ማረም በሚለው ስር  Byrne (1988) በፅሁፍ ውስጥ ከሆነ ተማሪዎች ብዙ ስህተቶችን በመስራታቸው  እንዲሸማቀቁ ከጓደኞቻቸው ያነሱ እንደሆነ አድርገው ራሳቸውን ስለሚቆጥሩ በመምህራቸው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በማለት ከገለፁት ሀሣብ ጋር ይገናኛል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የተፈጠሩ ስህተቶችን በመጠቆም እመለከታለሁ ያሉትን ደግሞ  በክለሳ ድርሳኑ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች ምልክቶችን በመጠቆም ስህተቶችን ማመልከት ከሚለው ስር ምልክቶችን በመጠቆም ስህተቶችን ማመልከት የምጋቤ ምላሽ ዘዴ ተማሪዎች

በሚጽፉበት ውስጥ ያለውን ስህተት አምነው በመቀበልየሚቀጥለው ፅሁፋቸው ችግራቸውን ቀርፈው እንዲፅፉ ከማድረጉም በተጨማሪ የተማሪዎችን አእምሮ በማይነካ መልኩ ስህተቶችን መጠቆሙ በሚቀጥለው ፅሁፋቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ከሚለው የምሁራን ሀሳብ ጋር በመያያዙ እና ይህንን መምህራንተግባራዊ ከደረጉ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እንደሚያዳብር መገመት ይቻላል፡፡

ተራ ቁጥር 8 ተማሪዎች መምህራን ለሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች ምን ስሜት አላቸው ? ይበልጥ ተግባራዊና ንቁ ምላሽ የሚሰጡት ለየትኞቹ ነው? ለሚለው ቃለ መጠይቅ መምህር 1፣2፣3 መጥፎ ስሜት እንደሌላቸው ስህተታቸውንአይተው ለማስተካከል እንደሚችኩሉ መምህራን እንዳያዘገዩባቸው ይፈልጋሉ፡፡ መምህር 4 የተማሪዎቼ ስሜት ጥሩ ነው እኔም ሁሉም ተማሪዎች ንቁ ምላሽ እንዲሰጡኝ መንገድ አመቻቻለሁ መመርህር 5 ጥሩ ስሜት አላቸው ምክንያቱም ሞራላቸው በመጠበቅ እንዲያስተካክሉ ስለሚደርግ ይመስለኝል ይበልጥ ንቁ ምላሽ የሚ,ሰጡኝ ግን ለስርዐተ ነጥብና ለቅርፅ ማስተካከል ነው፡፤ መምህር 6 ጥሩ ስሜት አላቸው ንቁ ምላሽ  የሚሰጡት  መምህራን በማበረታታት ስህተታቸውን ሲያሳዩዋቸው ነው፡፡  ከላይ በቀረበው ምልልስ የምንረዳው ተማሪዎች መምህራን ለሚሰጧቸው ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያላቸው ስሜት እንደ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ እንደሚለያይ የሚያሳይ ሆኖ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት  ምጋቤ ምላሽ ሙያዊ ስነ ምግባርን የተላበሰ ከሆነ መምህሩ ተማሪዎቹ ማወቅ ያለባቸውን ችሎታ እንዲጠቀሙና እንዲፅፉ የሚረዳቸው መሆኑን ያሳያል በተጨማሪ ተማሪዎች ንቁ ምላሽ የሚሰጡትም ለስርዓተ ነጥብና ለቅርፅ መሆኑ ደግሞ በሂደት ሌላውንም የሚሰጣቸውን ምጋቤ ምላሽ በዚሁ አንፃር እያስተካከሉ ጥሩ ድርሰት የሚጽፉ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በውጤት ትንተናው በመጀመሪያው የታየው በመምህራን ታርመው  የተመለሱት የድርሰት መፃፍ ፈተናዎች ከምሁራን አመለካከት አንፃር ያላቸውን ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ትንተናም መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማደበር በኩል የሚያመጣው ለውጥ ከፍተኛ ሆኗል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ይመስላል፡፡

በዚህ መሰረት መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾችየመጻፍ ችሎታቸውን በማዳበር በኩል ያለውአስተዋፅኦ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ትንተናው አሳይቷል፡፡ ይህውም (ኪህ1990) እንደሚገልፀው ምጋቤ ምላሽ ለፅህፈት ሂደታዊ አቀራረብ መሰረታዊ አላባ ነው፡፡ ተማሪው (ፀሀፊው) ጽሁፉን እንዲከልስ መምህሩ የሚሰጠው የመረጃ ግብአት ነው፡፡ ከሚለው ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

በተጨማሪ ከምሁራን ሀሳብ ተሻሽሎ በተዘጋጀው ፅሁፍን ለማረም የሚረዱ የችሎታ መመዘኛዎች የነጥብ አሰጣጥ አንጻር የተማሪዎችን ተከታታይ የፅሁፍ ድርሰት በማፃፍ ከጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በፊት ካለው ፅኁፍ ይልቅ ከጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በኋላ ተማሪዎች በድርሰት መፃፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል እንደታየ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ከሚሰጣቸው የሙከራ ቡድንና ምንም አይነት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ከማይሰጣቸው ጥብቅ ቡድኖች መካከል የድርሰት መፃፍ መሻሻል የታየው የፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በሚሰጣቸው የሙከራ ቡድን ሲሆን በጥብቅ ቡድኑ ግን ጽሁፋዊ ምጋቤ መላሽ ባለማግኘታቸው የድርሰት መፃፍ ችሎታቸው አነስተኛ መሆኑን (እንዳልተሸሻለ) አሳይቷል፡፡ በተጨማሪ በፅኁፍ መጠይቅ መሠረት አብዛኛው ተማሪ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመጻፍ ችሎታቸውን እንዳሻሻለላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ መምህራንም በቃለ መጠይቁ መሰረት ተማሪዎች በተከታታይ ምጋቤ ምላሽ እየተሰጣቸው ስህተታቸውን ሲያርሙ የድርሰት መፃፍ ችሎታቸው እየተሸሻለ እንደሚሄድ ገልፀዋል፡፡

ከትንታኔው ውጤት በመነሳት መምህራን ከሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሾች ውስጥ ተማሪዎች ፈጥነው የሚያስተካክሉት በቅርጽ ዙሪያ ያሉትን እንደ ስርዓተ ነጥብና ቅርጽ ያሉትን እንደሆነ እና ሌሎቹንም በሂደት እያስተካከሉ እንደሄዱ ገልጿል፡፡ መምህራን ደግሞ ትኩረት ሰጥተው እንዲያስተካክሉ የሚያደርጉት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሻቸው ይዘትና አደረጃጀት እንዲሁም ቅርጽ ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ ስር እንደተገለፀው ይዘታዊ ምጋቤ ምላሽ እውቀት ተኮር ነው፡፡ በድርሰት ይዘት ላይ የሚሰጥ ምጋቤ ምላሽ ነው፡፤ በድርሰት አደረጃጀት በሀሳብ ተገቢነት በማስረጃ አደጋገፍ በማብራራት በሎጂካዊ የጭብጥ አስተዳደግ ፣ በሀሳብ ተያያዥነት ተከታታይነትና ሀሳቦችን በግልፅመፃፍ ወዘተ ላይ ያተኩራል፡፡

በተጨማሪ በመጀመሪያው ወይም በቅድመ ድርሰት ፈተና በተጠኝ ቡድኖች በ9ኛA እና በ9ኛB መካከል ተመጣጣኝ ስህተተት እንደታየባቸው ትንታኔው የሚያሳይ ሲሆን

በተከታታይ በአንድ ርዕስ የሙከራ ቡድኑም የጥብቅ ቡድኑም ድርሰት እንዲፅፉ ከተደረጉ በኋላ ለሙከራ ቡድኑ በየ15 ቀን እንዲፅፉ ለተሰጠቸው 4 ድርሰቶች ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ እየተሰጣቸው ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ በማድረግ የተሻለ ድርሰት ሲፅፉ የጥብቅ ቡድኑ ደግሞ እንደሙከራ ቡድኑ በየ15 ቀን እንዲፅፉ ለተሰጣቸው 4 ድርሰቶች ምንም አይነት የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ሳይሰጣቸው የፃፉት የመጨረሻ ድርሰታቸው ከመጀመሪያው ድርሰታቸው ጋር ሲነፃፀር መሻሻል እንዳልታየበት ትንተናው ያሳያል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተከታታይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች ቢደረግላቸው የድርሰት መፃፍ ችሎታቸው እንደሚሻሻል ነው፡፡

በተጨማሪ ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሾችበተማሪዎች ድርሰት ፅሁፍ ላይ ሲቀመጡ እንደተማሪዎች ስህተት መጠን እንደሚለያይ እንዲሁም ተማሪው ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመው ስህተት በርካታ ከሆነ የተወሰኑትን ጠቅሶ እንዲያስተካክል ማድረግ ሌሎቹ ላይ ደግሞ ምልክት በማስቀመጥ ለሚቀጥለው የተጠቀሱትን ሲያስተካክል ሌላውን በመጥቀስ ቀስ በቀስ የተማሪዎችን የድርሰት መፃፍ ችሎታ በማዳበር በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው መረጃው ይገልፃል፡፡

